# ቅጣትና ኅብረተሰብ ፤ ዕድገታዊ አመለካከት

በፋሲል ናሆም

## I በኅብረተሰብና በቅጣት መካከል ያለው ግንኙነት

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የቅጣቱ ስልትና ዓይነት[1] መደጋገሙና ክብደቱ፡ በአንድ አፈንጋጭ (ወንጀለኛ) ላይ ቅጣቱን ለመፈጸም የሚደረገው ሂደት ህብረተሰቡ ራሱ ምን እንደሚመስል አመልካች ነው ። ኅብረተሰብ ዋጋ የሚሰጣቸው ወጐችና ልማዶች ሁሉ በሚጥላቸው ቅጣቶች ውስጥ ተጠቅለው ይገኛሉ ። አንድ ሕብረተሰብ በሕይወቱ ውስጥ ለምን ነገር ትልቅ ግምት እንደሚሰጥ ፤ ትልቅ ግምት ከሚሰጣቸው ነገሮች የቱ ከየትኛው እንደሚበልጥ ፥ እንደዚሁም ኅብረተሰቡ እነዚህን ዋጋ የሚሰጣቸውን ወጐችና ልማዶች የቱን ያህል እንደሚንከባከባቸው ፤ በአንድ አፈንጋጭ ላይ በሚጥለው ቅጣት በግልጽ ይንጸባረቃሉ ፥ ስለሆነም ቅጣት አንድ ኅብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ ፥ የፈጠራ ችሎታ ያለውና ተራማጅ መሆንና አለመሆኑን መለኪያ ሆኖ ያገለግላል[2] ።

ተስፋ እንደምናደርገውና በምንም ዓይነት ቢሆን ኅብረተሰብን በቁጥር ስሌት አማካይነት በሚያጠኑ የህብረተሰብ ሳይንስ ሊቃውንት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ቢችልም ፥ ኅብረተሰብ ዋጋ የሚሰጣቸውን ወጐችና ልማዶች በቁጥር ስሌት መግለጽ ከፍተኛ ትክክለኛነት ባለው ቁጥራዊ አሠራር ማህበራዊ ማጠቃለያዎች መስጠት ከዚህ ጽሁፍ ዓላማ ውጭ ነው ። እዚህ ላይ የጸሐፊው መጠነኛ ዓላማ ቅጣትን በአጠቃላይ መልኩ በማየት በዚህ ወሳኝ መስክ ውይይትን ለመቀስቀስ ነው ። ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ከሌላው ዓለም ጋር በማነጻጸር ሆኖ ሳለ ዝርዝር ሁኔታ መስጠት በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ልምድ በብዛት ሰፍሯል[3] ። የዚህ ጽሑፍ ርዕስ በኅብረተሰብ ሳይንስ ላይ በመሆኑ በዚህ መቅድም ላይ ስለ ኅብረተሰብ ሳይንስ በመጠኑም ቢሆን ማውሳት አግባብነት ያለው ሳይሆን አይቀርም ። የኅብረተሰብ ሳይንስ አዝማሚያ በአንዳንድ ክፍሎች ዕድገት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ሰው ለእንጀራና በእንጀራ ብቻ ይኖር ይመስል በጠባቡና በደረቅ ኢኮኖሚያዊ መስኩ ማጥናት ሆኖ ይታያል ። ዕድገት በተለይም የሰው ማህበራዊ ዕድገት በሰው ልጅና በኅብረተሰብ ዕርምጃ አጠቃላይ ዕውነታ ላይ ከእጅ ወደ አፍ እስከ ምርት መቅረፍረፍ ያለውን ቁስ አካላዊ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ከማይረባ እምልኮ እስከ ሳይንሳዊ ዕውቀትና ከአውሬነት ባሕርይው እስከ ጨዋነት ባሕርይው ባለው ዕድገቱ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል ። እነዚህ የዕድገት መስኮች የተያያዙ ቢሆኑም በጠባቡ የተወሰኑ ግምት ማየት ያልተለመደ አይደለም ፥ ይኸውም አንዱ የዕድገት ዘርፍ ኖሮ ሌላው ሳይኖር ይችላል ። ጉዳዩን በምሳሌ ለማስረዳት የዘር መድልዎ አገዛዝ የሰፈነበትን ደቡብ አፍሪካን መጥቀስ ይበቃል ። የዕድገት ደረጃዋ በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ከእጅ ወደአፍ ኢኮኖሚ ይልቅ ወደዳበረ ኤኮኖሚ ይመደባል ። ይህም ሆኖ ግን የአብዛኛው ዜጐቹን አያያዝ እንዲሁም ስለዘር ልዩነት ያላትን አጠቃላይ አመለካከት ስናይ የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት መቆጠር ያለበት እንደሰለጠነ ሆኖ ሳይሆን ኋላ ቀርና የአረመ

ኔነት ባህርይ እንዳልተለየው ሆኖ ነው ። የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች በኢኮኖሚ አቋማቸው ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተሻሉ ሊሆኑ መቻላቸው የሐቁ አንድ ገጽታ ብቻ ነው ። ሌላ የሐቁ ገጽታ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ጥቁር ሠርቶ አደር ላይ ኢሰብአዊ ተጽዕኖ በሚያደርጉ ብዙ ሕጎች ውስጥ ይገኛሉ ።

የ1911 ብሔራዊ የሠራተኛ ጉዳይ ድንጋጌና ማንኛውም ጥቁር በኮንትራት እንዲሠራ የሚያስገድደው ፤ የ1964 የባንቱ የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ፤ የ1913 ብሔራዊ የመሬት ስሪት ሕግና ጥቁር አፍሪካውያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ ሀብትነት የሚከለክለው የ1936 የመሬት ሕግ ፤ የ1911 የማዕድናትና የሥራዎች ሕግና ፤ አውሮፓውያን ካልሆኑት በአንድ ሙያ የመሰልጠን ዕድልን የሚዘጋው የ1944 ሥራ መልመጃ ውል ሕግ የአፍሪካውያን ነባር መኖሪያ ለጥቁሮች ከተ ከለለው ሥፍራ ውጭ እንዳይሆን የሚደነግገው የ1964 የባንቱ ሕግጋት ማሻሻያና ለባንቱ አገር አስተዳደርና የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትሮች ማንኛውም ጥቁር በማን ኛውም ቦታ ፤ በማንኛውም አሠሪ ፤ ለማንኛውም ዓይነት ሥራ እንዳይቀጠር ለመከ ልከል የሚያስችላቸው ሥልጣን የሚሰጠው የ1970 የባንቱ ሕግጋት ማሻሻያ[4] ከብዙዎቹ አድላዊ ሕጎች ጥቂቶቹ ናቸው ። የዓለም ሕዝብ አስተያየት ከሶሻሊ ስት ጐራ እስከ ካፒታሊስት ጐራ ታዳጊውን ዓለም ጨምሮ በደቡብ አፍሪካ ላይ ጠንካራና ያላሰለሰ ውግዘት በማሰማት ላይ መሆኑ የሚያንጸባርቀው የሰውን ልጅ ዘላቂ ፍላጐት ይኸውም የሰው ማኅበራዊ ዕድገት ማለትና መሆን ያለበት ሌላ ሳይሆን በአጠቃላይ መልኩ የሰብአዊ ክብር ከፍ ማለት ነው ።

በሰው ህልውና እንጀራ አስፈላጊ ቢሆንም ፤ የሰው ልጅ እድገት በእንጀራ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ በምንም ብቸኛ ነገር የተወሰነም አይደለም ። ታዲያ ፤ ይህ ማለት ደግሞ ስለሰው ማህበራዊ እድገት አጥጋቢ ቲዎሪ እንዲሁም ለታ ለመ ተግባር መሰረት ሆኖ ሊያገለግል ከሚችል ትክክለኛ ማጠቃለያ ላይ ለመ ድረስ የሰውን ልጅ የሚመለከቱ መስኮች ሁሉ መጠናት አለባቸው ። የሰውን ማኅበራዊ ዕውነታና ፍላጐት ፤ በኋላ ቀርነት እስከ ዕድገት ያለውን ጠመዝማዛ ጉዞ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲያንጸባርቅ ከተፈለገ ጥናቱ የግድ ብዙ ሁኔታዎችን ያቀፈ መሆን አለበት ። «ቅጣትና ሕብረተሰብ» የሚለው የመጀመሪያ ጥናት የቀ ረበውም በዚህ አግባብ (መሠረት) ነው ።

## II ፍትሕና የቅጣት ዓላማዎች

ፍትሕ በአንድ በተወሰነ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መዋቅር (ሥርዓት) ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ መንከባከብና መጠበቅ ጋር አንድ ሊመስል ይችላል[5] ቅጣት የሚፈጸመው ይህ አስፈላጊና ምቹ የሆነው ሚዛን በሚቃወስበት ጊዜ ድሮ የነበረውን ሥርዓት ለመገንባትና ለወደፊቱ ያለውን ሁኔታ ሳይቃወስ ለመ ጠበቅ ነው ። አባባሉን ምሳሌ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል ። አንድ ሌባ ከአንድ ገበሬ አንዲት ላም በሚሰርቅበት ጊዜ ያለው ሁኔታ ይናጋል ፤ ሁኔታዎች እንዳሉ እንዲቀጥሉ መተው በፍትሕ ላይ ወንጀል መፈጸም ይሆናል[6] ። ኅብረተሰቡ አንድ ዓይነት ዕርምጃ መውሰድ አለበት ፤ ግን ምን ዓይነት ? የላሟ መመለስ ፤ ማለትም የቀድሞውን ሁኔታ መመለስ ወይም ጥፋተኛው በደል ላደረሰበት ሰው ተመጣ ጣኝ ዋጋ እንዲያስረክብ ፤ ለምሳሌ ተመሳሳይ ላም ወይም ገንዘብ ማለትም በተ ቻለ መጠን ከድሮው ጋር ተቀራራቢ የሆነ አዲስ ሥርዓት መገንባት ከግዙፋዊ አመለካከት አኳያ ያለውን ሁኔታ ሊያረካ ይችል ይሆናል ። ነገር ግን ግዙ ፋዊ ካልሆነ አመለካከት አኳያ አሁን ታሪካዊ ዕውነት የሆነው ያለውን ሁኔታ

ያናወጠው ድርጊት ትዝ ይለናል ። ለወደፊቱ በዚሁ ወንጀለኛ እንደዚሁም የሱን አርአያ በሚከተሉት ተመሳሳይ ወንጀለኞች የድርጊቱ መፈጸም አደጋ ይታየናል ። የደረሰው ቁስአካላዊ ጉዳት ወደነበረው ሁኔታ ከተመለሰ በኋላ ወንጀለኛው በነጻ እንዲሄድ መፍቀድ አሁን ያለው ሁኔታ ለወደፊቱ እንዲናጋ መጋበዝ ይሆናል ። ለወደፊት ሊደርስ የሚችለውን የጸጥታ መናጋት ለመቀነስ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ከነበረበት ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በከፋ (በጐጂ) ሁኔታ ላዒ እንዲገኝ ሊያደርገው የሚችል ግዴታ በወንጀለኛው ላይ መወሰድ አለበት[7]።

ይህን የመሰለውን አባባል ሁለት የተያያዙ ጥያቄዎችን ሊያነሳ ይችላል ፡ ይኸውም 1ኛ. የቱን ያህል መጐዳት አለበት ? እና 2ኛ. ይህን ለማድረግ ኅብረተሰብ ምን ዓይነት ዕርምጃ መውሰድ አለበት ? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው ። በጥንቱ (ጊዜ) ዘመናት (በጣም ጥንታዊ ያልሆኑ ኅብረተሰብቦችም ጭምር) የበቀል ፍርድ (LEX TALIONI)[8] ማለትም ዐይን ያጠፋ ዐይኑ ይጥፋ ፣ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይውለቅ በማለት የተዘጋጀና አጠቃላይ የሆነ ፍትህ ይሰጡ ነበር ። ሌሎች ማህበሮች እንደዚህ ቀላልና ቀጥታ የሆነ መልስ ላይሰጡ ይችላሉ ። በዚህ እስቸጋሪና ውስብስብ መስክ እንደዚህ ያለ መልስ መስጠት አለባቸው ብለንም ሀሳብ እና ቀርብም ። ሕብረተሰብ በቅጣት ምን ጥቅም እንደሚያገኝ (ግብ እንደሚመታ) ካላወቁ ውጤቱ አሳዛኝ ይሆናል ።

በመሆኑም ሕብረተሰብ ሁልጊዜ የቅጣት ጥቅም ምንድነው ከሚለው ጥያቄ ጋር እንደተፋጠጠ ነው ። ችግሩን የማስወገጃ አንዱ መንገድ ኅብረተሰብ የነበረውን ሁኔታ ወደ ቦታው ለመመለስ ወይም ያለውን ሁኔታ ከወደፊት ሁከት ለመጠበቅ የደረሰውን ሁኔታ (የተፈጸመውን) ከምን አኳያ እንደሚመለከተው በመወሰን ሊሆን ይችላል ።

ኅብረተሰብ ማተኮር ያለበት በደረሰው ሁኔታ ላይ ነው ? ወይስ ጉዳት በደረሰበት የኅብረተሰቡ አካል ላይ ነው ፣ ወይስ ደግሞ በአፈንጋጩ ላይ ወይስ በኅብረተሰብ አጠቃላይ ፍላጐት ላይ ነው መሆን ያለበት ? ጥያቄውን ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስቀመጥ ኅብረተሰብ በልቦናው ውስጥ ምን ዓላማ ሊኖረው ይገባል ? ጉዳት የደረሰበት ሰው ላይ ማተኮር መሆን አለበት ? አስፈላጊ ከሆነም በበቀል የቆሰለውን ጉዳት የደረሰበትን ሰው ስነልቡናዊ ወዘና እስከ ማርካት ድረስ ማለትም ክፉን መበቀል እስከሚለው መሄድ አለበት ? ወይስ ከዚህ ትንሽ ለየት ባለ አመለካከት በደረሰው ሁኔታ ላይ ማተኮርና አጸፋውን ለመመለስ መሞከር ፣ ለምሳሌ ነፍስ ግዳይን በሚመለከት ረገድ «ያለደም ስርየት የለም» ማለት አለበት ? ወይስ ኅብረተሰብ አፈንጋጩ ለምን እንዳፈነገጠ ለመረዳትና እሱን ወደ ኅብረተሰቡ ለመመለስ ብሎም ኅብረተሰቡ እርሱና እርሱን ከመሰሉ አፈንጋጮች ወደፊት እንዲጠበቅ ፣ ኅብረተሰብ እንደዚህ ላለው ማፈንገጥ ዋናውን መንስኤ ለማጥፋት እንዲችል በአፈንጋጩ ላይ ማተኮር አለበት ?

ኅብረተሰብ አንድን አፈንጋጭ በመቅጣት ለማግኘት የሚሞክራቸው ግቦች (ውጤቶች) በሶስት ታላላቅ (ሠፋፊ) ፈርጆች ሊጠቃለሉ ይችላሉ ። ከባሪያ ሥርዓት እስከ ፊውዳሊዝምና አሁን እስካለንበት ዘመን ባለው የሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ውስጥ የሚታወቀው የመጀመሪያው የቅጣት ግብ ክፉን መበቀል የሚለው ነው ። ከጥንት ኅብረተሰብ ቴዎሪያዊ ጥናት ጀምሮ ከአውሬነት እስከ ጨዋነት ባለው የሰው ማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ክፉን በክፉ መበቀል የሚለው የቅጣት ግብ ብዙም ተቀባይነት የሌለው ነው ። የሌክስታሊዮን ፍልስፍና ተከታዮች ክፉን በክፉ መበቀል የሚለውን የቅጣት ግብ በመጠቀም ይታወቁ ነበሩ ። በአሁኑ ዘመን

በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ዋዜማ በብዙ ዘመናዊ ኅብረተሰቦች ያለውን ልዩ ልዩ ዓይነት ቅጣት በሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች ስንመለከት አሁንም ቢሆን የሰው ልጅ እራሱን ከፉን በክፉ መበቀል ከሚለው የቅጣት ግብ ማላቀቅ እንዳላበት ግልጽ ይሆናል ።

ኅብረተሰብ በቅጣት አማካይነት ለማግኘት የሚሞክረው ሁለተኛው ግብ፥ ወንጀለኛውን ማረምና ወደኅብረተሰቡ መመለስ ሲሆን ፣ ይህ ግብ ግን ከኅብረተ ሰቡ ጋር መቶ በመቶ ገና ያልተዋሐደ ሆኖ ይገኛል ። ይህ ግብ በሰው ልጆች ዘንድ ገና አስፈላጊውን ትውውቅ ያላገኘና ፣ በመከሰት ላይ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ በሥነ አዕምሮ ሳይንስ በኩል የሳይንሳዊ ዕውቀት መስፋፋት በቅጣት ላይ ያለ ጥርጥር ዘላቂ ተጽዕኖ ይኖረዋል ። ዕርማት በቅጣት ዓላማነቱ ኅብረተሰቡንም ሆነ አጥፊውን በጥሩ አኳኋን ይጠቅማል ። ኅብረተሰብ በቅጣት አማካይነት ሊያገኘው የሚሞክረው ሶስተኛው ግብ ማስጠንቀቂያ ሲሆን አጥፊውን ለወደፊቱ በማስጠንቀቅና ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ በማስጠንቀቅ በሁለት መንገድ ያገለግላል[9]። ግለሰባዊ ማስጠንቀቂያ ወንጀለኛውን ወንጀል ዘላቂ ቁምነገር እንደሌለው በማስተማር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን በአጠቃላይ ሁኔታው እጅግ በጣም ብዙ ነገር የሚጠይቅና ስቃይ የተሞላበት እንደሆነም ጭምር ነው ። ግለሰባዊ ማስጠንቀቂያ ወንጀለኛውን በለስላሳ ማግባባት ሳይሆን ኃይል በተሞላው ጠንካራ ክንድ እንደገና ወንጀል መፈጸም ረብ እንደሌለው በማሳመን ልማደኛ ወንጀለኛነት ለማሸነፍ ይሞክራል ። እንደዚሁም በአደባባይ ላይ የሚፈጸመው ቅጣት ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ ለማስተማር ያገለግላል ። ስለዚህ የቅጣት ግብ ለወደፊት ወንጀል ሊፈጽሙ ከሚችሉ ሰዎች የወንጀል ውጤቱ መራራ እንደሆነ አጠቃላይ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ላይ ያተኩራል ።

ማንኛውም የቅጣት ዓይነት ቢሆን ከሕብረተሰብ ደህንነትና ጥበቃ ሌላ በቂ ምክንያት ሊኖረው አይችልም ። ኅብረተሰብ ደግሞ ቅጣትን ከወንጀለኛና ወደ ፊት ወንጀለኛ ሊሆኑ ከሚችሉ ግለሰቦች አንጻር አስተዋይ ትኩረት በማድረግ በይበልጥ ራሱን ይከላከላል ። በዚህ አባባል ትክክለኛነት ላይ የተመሠረቱ በር ከት ያሉ ግምቶችና ምሳሌዎች ከተቻለም ዘላቂነት ያላቸው ማጠቃለያዎች (መደ ምደሚያዎች) መነሳታቸው አይቀርም ። አንዱ መሰረታዊ ግምት በኅብረተሰብ ብቻ ሳይሆን በወንጀለኛውም አስተዋይነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ኅብረተሰብ ሊያስተላልፍ የሚሞክረው ማንኛውም መልዕክት በትክክል ከወንጀለኛው ሊደ ርስ የሚችለው ወንጀለኛው አስተዋይ ከሆነ ብቻ ነው ። በሌላ አነጋገር በአንድ ሰው የሚፈጸመው ቅጣት ሊያስተውል የሚችለውን ያህል መሆን አለበት ፤ የሚ ሠራውን ለማወቅ የማይችል ወይም የፈጸመው ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ለመረዳት የማይችል ሰው የፈለገው ሌላ ነገር ሊፈጸምበት ቢችልም ቅጣት ሊፈጸምበት አይገባም[10]።

ሌላው ግምት ደግሞ አንድ ሰው ቅጣት የሚፈጸምበት ግዴታውን ከመወ ጣት ላይ እያለ በራሱ ጥፋት በኅብረተሰቡ ላይ ወንጀል ሲፈጸም ነው ። ጥፋት አንድ ሰው በኅብረተሰቡ ላይ ያለውን መጥፎ አስተያየት የሚያመለክት ረቂቅ ቃል ነው ። እንደዚህ ያለ መጥፎ አስተያየት ደግሞ ሆን ተብሎ የሚሰወድ ሊሆን ይችላል ፣ ይኸውም እያወቀና የሚያስከትለውን ጉዳት እየተረዳ ውጤቱን በመቀበል ጸረ ኅብረተሰብ ድርጊት መፈጸም ሊሆን ይችላል ። ወይም ደግሞ በቸልተኛነት ሊሆን ይችላል ። ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ሊያደርጋቸው የሚገቡትን

ጥንቃቄዎች ባለማድረግ ሊሆን ይችላል ። ኅሊናዊ (አዕምሮአዊ) የጥፋት መለኪያ፣ ሆን ብሎ (አውቆ) ማጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይኖር በአጋጣሚ የደረሰ ጸረ ኅብረተሰብ ድርጊት በቅጣት ክልል ውስጥ መውደቅ የለበትም[11]።

ትክክለኛ የቅጣት አሠራር የአንድን ወንጀለኛ ግለሰባዊ ፍላጐቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ለአንድ የተወሰነ ወንጀለኛ በግፈኛነቱና በሚወስደው ዕርምጃ ደረጃ ተስማሚ የሆነ ለዚያ ወንጀለኛ በተለይ የተዘጋጀ ቅጣት ይወስናል ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ኅብረተሰብ ሳይንሳዊ የሆነ አመለካከት ሊኖረው ይገባል ፣ ማለትም በሁኔታዎች ግንዛቤና ትንታኔ ላይ የተመሠረተ ማጠቃለያ ላይ መድረስ ይኖርበታል ።

በመጨረሻ ኅብረተሰብን ከወንጀል ለመከላከል በወንጀለኞችና ወደፊት ወንጀለኞች ሊሆኑ በሚችሉ ግለሰቦች ላይ ትክክለኛ (አስተዋይ) ትኩረት ማድረግ በቀል ትክክለኛ የሆነ የቅጣት ግብ እንዳልሆነ ያሳየናል ። ይህም ማለት ማስጠንቀቂያ (ማህበራዊና ግለሰባዊ) እና እርማት ብቻ የቅጣት ትክክለኛ ግቦች በመሆን ይቀራሉ ። ሆኖም ቅጣት ጠቃሚና ገንቢ ለመሆን ሁለት መለኪያዎችን ማለፍ አለበት ፣ ለማስጠንቀቂያነትና ለዕርማት ማገልገል አለበት ። አስጠንቃቂና አራሚ ያልሆነ ማንኛውም ቅጣት ፍቱንነት ስለሌለው በኅብረተሰቡ ውስጥ ቦታ ሊኖረው አይገባም ። እንዲያውም እነኝህ መለኪያዎችን የማያሟላ ቅጣት በአማራጭ ሊተካ ይገባዋል ። አንድ ዓይነተኛ አርእያነት ያለው የቅጣት አሠራር ሁለቱንም የቅጣት ግቦች ማስጠንቀቂያነትንና አራሚነትን በተለያየ ደረጃ መያዝ ይኖርበታል ። ማስጠንቀቂያና ዕርማት በአንድ ቅጣት ውስጥ የሚኖራቸውን ተመዛዛኝነት የሚወስኑት ነገሮች የወንጀለኛው አደገኛ ባሕርይ ፣ የወንጀሉ ጸባይ እንዲሁም ወንጀሉ እንዲፈጸም ያነሳሱትና ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታዎች ናቸው ።

ቅጣት የሚያስከትለው ማህበራዊ ጉዳት መናቅና መታለፍ የሌለበት አስፈላጊ ነገር ነው ። ከማስጠንቀቂያነትና ከአራሚነት ያለፈ ቅጣት የሚጭን አደገኛ የቅጣት አሠራር ፣ አፈንጋጩ እንደ ጤነኛ የኅብረተሰብ አባል የሚቻለውን ሁሉ ለኅብረተሰቡ አስተዋጽኦ እንዳያደርግ በመላ ሕይወቱ በአካልና በአእምሮ ሽባና ስንኩል እንዲሆን ስለሚያደርግ አስፈላጊ አይደለም ። በዚህ ጊዜ የሚቀጣው አፈንጋጩን ብቻ አይደለም ። ነገር ግን አፈንጋጩን ከመጠን በላይ ከመቅጣቱም አልፎ ኅብረተሰቡንም ጭምር ይቀጣል ። ቅጣት የሚያስከትለው ማኅበራዊ ጉዳት በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተውና ጫና የሚሆነው ለተቀጭው አፈንጋጭ የቅርብ ቤተሰቦችና እንዲሁም ወዳጆች ነው ። ለምሳሌ ያህል ጥገኞቹ የሚበሉትና የሚቀምሱት ሳይሰጣቸው የአንድ ቤተሰብ አስተዳዳሪ መታሰር በወንጀለኛው ላይ ብቻ የተወሰደ ዕርምጃ ሳይሆን በንጽሕ ጥገኞች ላይ ጭምርም የተወሰደ ነው ። በመሆኑም በብዝበዛ ላይ የተመሰረቱና ትክክለኛ ያልሆነ ዕርምጃ የሚወስዱ ኅብረሰቦች ለብዙ ጊዜ የሚቆይ መጥፎ ውጤት ያለው ተግባር ይፈጽማሉ ።

የባሕላዊ ቅጣት ዓይነቶች ጥናት የትኞቹ የቅጣት ግቦች ከፍተኛ ግምት እንደተሰጣቸው በትክክል ያሳያል ። ቀደም ሲል እንዳስገነዘብነው ሁሉ ቅጣትን አንድ ኅብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ የፈጠራ ችሎታ ያለውና ተራማጅ መሆንና አለመሆኑን እንደ መለኪያ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርገዋል ። በማስከተል በጥቂት ባሕላዊ የቅጣት ዓይነቶች ላይ እናተኩራለን ።

## III ባሕላዊ (ልማዳዊ) ቅጣቶች

### ሀ. እሥራት

ኅብረተሰብ ከድሮ ጀምሮ በአንድ አፈንጋጭ ላይ የሚወስዳቸውን ልዩ ልዩ የቅጣት ዕርምጃዎች ስናስብ ቶሎ ብሎ በአዕምሮአችን የሚመጣው የቅጣት ዓይነት እሥራት ነው ። በእርግጥም በዘወትር የቋንቋ አጠቃቀም ቅጣትና እስራት ተመሳሳይ ናቸው ። እስር ቤቶች የመላው ዓለም መንግሥታት መለያ ባሕርይ ስለሆኑ አንድ እስርቤት የአንድ መንግሥት አካልና አምሳል ፣ መንግሥት ሲመሰረት ጀምሮ የነበረ ነባራዊ ተቋም ነው ብሎ ሊያስብ ይችል ይሆናል ። ምንም እንኳ መቼና የት እንደተጀመረ ለመናገር አስቸጋሪ ቢሆንም እሥራት በጣም የጥንት ልማድ እንደነበር አያጠራጥርም ። ኅብረተሰብ ለጊዜው በአፈንጋጮች ላይ ምን ዕርምጃ መውሰድ እንዳለበት ባለማወቁና የሚወሰደውን ዕርምጃ እስኪወስድ ድረስ ባዶ ቤት ውስጥ ይቆልፍባቸው ስለነበር እሥራት በዚህ ዓይነት ተጀመረ የሚል ቴዎሪ ለመንደፍ መሞከር በጣም ድፍረት (ማጋነን) ይሆን ? ሌላ የተሻለ ሃሳብ ሲጠፋ ይህ ጊዜያዊ እሥራት ደንበኛ የቅጣት ዓይነት እየሆነ ይመጣል ።

በልዩ ልዩ አገሮች ዛሬ እሥራት ቀላልና ጽኑ በመባል ይመደባል[12]። ቀላል እሥራት የሚባለው ከባድ ወንጀል ባልፈጸሙ ሰዎች ላይ ነው።ቀላል እሥራት በአንጻራዊ አመለካከት ሲታይ የአጭር ጊዜ ቅጣት ነው ። በሌላ በኩል ጽኑ እሥራት የሚባለው ለኅብረተሰቡ በጣም አደገኞች ናቸው ተብለው በሚገመቱ በጣም ከባድ ወንጀል በፈጸሙ ወንጀለኞች ላይ ነው ። ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው እስረኞች አብዛኛውን የሕይወት ዘመናቸው በማዕከላዊና በከፍተኛ ሁኔታ በሚጠበቁ እሥር ቤቶች ያሳልፉታል[13]።

እሥር ቤቶች በምንም ዓይነት የደስታ ቤቶች አይደሉም ፣ ኅብረተሰብ ብዙውን ጊዜ የመበቀያ መሣሪያ አድርጐ ስለሚጠቀምባቸው ይህ ሊያስደንቅ አይችምል ። በፊውዳል ኢትዮጵያ ስለእሥር ቤቶችና እስረኞች ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ኢትዮጵያን አቋርጠው ማለፍ ዕድል ባጋጣማቸው ተጓዦች የተነገሩ አንዳንድ መግለጫዎች እናገኛለን ።

ፖርቱጋላዊ ቄስ አልባሬዝ በድንኳን እሥር ቤት ውስጥ በእግረ ሙቅ ታሥረው ስለነበሩ እሥረኞች ይነግረናል ። እነዚህ እሥረኞች የራሳቸውን ቀለብ ብቻ ሳይሆን የሚጠብቋቸውን ዘበኞች ቀለብ ጭምር መቻል ይጠበቅባቸው ነበር ። እንግሊዛዊው ተጓዥ ሪቻርድ ባርቶን በ1850 የኢትዮጵያን እሥር ቤት «የቆሻሻ ጉድጓድ» ብሎ ጠርቷል ። ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ የአዲስ አበባን እሥር ቤት የተመለከተች ፐርሐም የተባለች ሌላ እንግሊዛዊት ተጓዥ እስረኞቹ ተረስተው በበሽታ እየማቀቁ በአስከፊ ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ፣ ይህም ሁኔታ በየጊዜው በበሽታ እየማቀቁ በአስከፊ የጤና ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ፣ ይህም ሁኔታ በየጊዜው በእሥር ቤቱ ተስቦ እያነሳ ብዙ እስረኞች እንዲሞቱ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ አሰቃቂ እንደነበር አመልክታለች[16]። እሥርቤቶች የፈለገውን ያህል መሻሻል አድርገዋል ቢባልም ብዙ ኅብረተሰቦች በዚህ ረገድ ያደረጉት እሥርቤቶችን ተቀባይነት ወዳለው ሰብዓዊ ተቋም ደረጃ ከፍ ሊያደርጋቸው የሚችል አነስተኛ መሻሻል ነው ።

አንድ ሰው እሥር ቤትን እንደ አስፈላጊ ፣ የእሥር ቤት መቅረትም በኅብረተሰቡ ላይ የአማልክትን ቁጣ ሊያወርድ እንደሚችለው አድርጎ ሊገምት ይችል ይሆናል ። እሥር ቤት በቅርብ መጠናት ይኖርበታል ። የቅጣት ጉዳይና

የቅጣት አስተዳደር የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሁም ይህን በገንዘብና በሰው ጉልበት አንጻር ብዙ ወጪ የሚያስከትለው አሠራር ለማካሄድ የሚደክመውና የሚጥረው ሁሉ የእሥር ቤትን ፍቱንነትና ጠቃሚነት የመመርመር ኃላፊነት አለበት ። የእሥር ቤት አሠራር ለወደፊቱ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሁለት ሳይንሳዊ መለኪያዎችን ማሟላት ይኖርበታል ። ይኸውም ቅጣት በማስጠንቀቂያነትና በማረሚያነት ማገልገል ይኖርበታል ። እሥራት አስጠንቃቂና አራሚ ነው ብሎ በሐሳብ መገመት ብቻ አይበቃም ። የእሥር ቤት አሠራር የማስጠንቀቂያነትና የአራሚነት ባሕርያት አሉት ከሚል በማስረጃ የተደገፈ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ትክክለኛ ሁኔታው መመርመር ይኖርበታል ።

## ለ. በአካል ላይ የሚደረግ ቅጣት

ሌላው ዓይነት ልማዳዊ ቅጣት እንዳጋጣሚ በአሁኑ ጊዜ ጨርሶ ባይጠፋም በመክሰም ላይ የሚገኘው በአካል ላይ የሚደረገው ቅጣት ነው ። በአካል ላይ የሚፈጸመው ቅጣት በብዙ ኅብረሰቦች በተለያየ መልክ ተከስቷል ። ወንጀለኞች እጅግ በጣም ኋላ ቀር በሆነ የህክምና አሠራር ማንኛውም ዓይነት የአካል መቆራረጥ ቅጣት ሲፈጸምባቸው ቆይቷል ። ለምሳሌ ያህልም በመዋሸት ጥፋተኛነት የተወሰነበት ሰው ምላሱ እንዲቆረጥ ሊፈረድበት ሲችል የሐሰት ምስክርነት በመስጠት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ዓይኑ እንዲወጣ ሲፈረድበት ቆይቷል ። በብዙ ኅብረተሰቦች አፍንጫ መፎነን ፣ ጆሮ መቁረጥ የወንድን ብልት መስለብና እጅና እግርን በመጥረቢያ መቆረጥ የተለመዱ ባሕላዊ ቅጣቶች ነበሩ ። በባሕላዊ ሕብረተሰቦች ሁሉ በፊውዳል ኢትዮጵያም ጭምር በአካል ላይ የሚፈጸመው ቅጣት የተለመደ የቅጣት ዓይነት ነበር ። እነዚህ ቅጣቶች ሲፈጸሙ ያጋጠሟቸው ተጓዦች ምስክርነታቸውንና የሁኔታውን አሻራ ትተውልን አልፈዋል ። በ1830 ዓ.ም. አንድ አገር ጐብኚ ንጉሡ የአንድ ሌባ አንድ እጅና ሁለት እግሩ እንዲቆረጥ አዞ ቅጣቱም ገበያ ውስጥ በአደባባይ መፈጸሙንና በኋላም እጅና እግሩን ያጣው ሌባ በዚያኑ ዕለት ማታ በጅብ መበላቱን የዓይን ምስክርነት ሰጥቷል[17]። በ19ኛው ምዕተ ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው አንድ ተጓዥ በጊዜው የነበረው ንጉሡ ጭካኔ የተሞላበት አሰቃቂ ቅጣት እንዲፈጸም ለምሳሌ የልማደኛ ሌባ እጅ እንዲቆረጥ ፣ የአሽሟጣጪና ምላስ እንዲቆረጥ ሲያዝ ትንሽ እንኳ ሰቅቅ አይለውም ነበር ሲል ገልጿል ። አንድ ጊዜ አንድ ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ ሲከላከል መንግሥትን የሚቃረን ነገር በመናገሩ ንጉሡ የጠበቃውን ምላስ አስቆረጠው[18]። አንድ ሌላ ሰው የአካል መቆራረጥ ቅጣት እንዴት ይፈጸም እንደነበር በመግለጽ የሚከተለውን ዘገባ አቅርቧል ።. ለሁለተኛ ጊዜ በሰረቀ ሌባ ላይ ይፈጸም የነበረው ቅጣት አንድ እጁን እንዲያጣ ማድረግ ነው ። የጥፋተኛነት ውሳኔ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ቆራጩ የወንጀለኛውን የእጅ አንጓ ጅማት ይጠመዝዝና በፋስ ይቆርጠዋል ። በዚህ ጊዜ ሴቶች ቅቤ በማሰሮ ያንጥራሉ ። የወንጀለኛው እጅ እንደተቆረጠ ወዲያውኑ ዱሹ በፈላው ውስጥ ይጨመራል ። በዚህ ዓይነት ደሙ እንዳይፈስ በማቆም የጥፋተኛው ሕይወት እንዳያልፍ ይደረግ ነበር[19]።

በኢትዮጵያ የአካል መቆረጥ ቅጣት የተወገደው በ1923 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕገ በመውጣቱ ነው ። ስለቅጣት የሚናገረው ምዕራፍ በግልጽ እንዳስቀመጠው በአካል ላይ የሚፈጸም ቅጣት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በግርፋት ፍርድ ላይ ብቻ እንዲወሰን ተደረገ ። ከዚህም ሌላ የ1923ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለጉዳዩ የተጨነቀበት ከመምሰሉም በላይ የግርፋት ቅጣት በቅርቡ እንደሚወገድ ቃል ገብቶ ነበር[20]። ይሁን እንጂ በ1949 ዓ.ም. አዲስና ከፍተኛ የወንጀለኛ መቅጫ

ሕግ ሲወጣ የተሰጠው የተስፋ ቃል ታጥፎ ግርፋት ከቅጣት ዓይነቶች አንዱ ሆኖ ወጣ[21]።የሕጉ አርቃቂ በረቂቁ ላይ ባይጨምረውም በፓርላማ የሞቀ ክርክር ከተደረገ በት በኋላ ተጨምሮ ገብቷል[22]።የሆነ ሆኖ አርቃቂው የመጨመሩን ተገቢነት እንዲህ በማለት ገልጿል ፡ «.  ስቃይን ሳይሆን የክብር መዋረድን በሚፈራ ኩሩና ጠንካራ ሕዝብ መካከል የግርፋትን ልማድ ጥቅም ዝቅ አድርጌ መገመት አይቻልም ፤ ግርፋት ባለው ሥነ ምግባራዊ ዋጋ ምክንያት ሕዝቡ እንደትልቅ ቅጣት አድርጐ ነው የሚቀበለው[23]። በመጀመሪያ የግርፋት ቅጣት ተወስኖ የነበረው ለከባድ ስርቆትና ለከባድ የውንብድና ወንጀል ብቻ ነበር[24]። ነገር ግን ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ብዙ ወንጀለኞች በግርፋት እንዲቀጡ ተደረገ ፤ ከእነሱም መካከል በንጉሡ ላይ የሚፈጸም ስድብ፡ ዘለፋና ስም ማጥፋት ይገኙበታል[25]። ቢሆንም የ1949 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የግርፋት ቅጣት የሚፈጸሙው ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 50 ዓመት በሆኑ ወንዶች ላይ ብቻ ከመሆኑም በላይ የግርፋቱም ቁጥር ከአርባ እንዳይበልጥና የሚፈጸመውም ወንጀለኛው ቅጣቱን የሚችል መሆኑ በሐኪም ከተመሰከረ በኋላ ነው ስለሚል በከፊል የዘመናዊነትና የመሻሻል ምልክት ይታይበታል[26]።

ግርፋት የበቀል ዓላማ እንዳለው አጠያያቂ አይሆንም ። አከራካሪ የሚሆነው ግርፋት የአራሚነትና የማስጠንቀቂያነት ዓላማ ነው በዚህ ጥያቄ ላይ የተደረገ ጥናትና ሁኔታውን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ባይኖርም ይህ ጽሑፍ ከግርፋት መሰረታዊ ዓላማ (በቀል) በመነሳት ግርፋት ከማስጠንቀቂያነትና ከአረሚነት አንጻር ያለውን ጥቅም ለመወሰን ይቸገራል ። በዚህ ረገድ ይህ ጽሑፍ ሊያቀርበው የሚችለው ኃሳብ ጠቃሚነቱ በሚያሳምን ሁኔታ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአካል ላይ የሚፈጸመው የግርፋት ቅጣት እንደ ኋደኛው የአካል መቆራረጥ ቅጣት መቅረትና መረሳት የለበትም ወይ ከሚል የተለየ አይሆንም[27]።

ሐ. <u>የሞት ቅጣት</u>

የሞት ቅጣት በሁሉም ሕብረተሰቦች ዘመናት ከፍተኛ ቅጣት ሆኖ ቆይቷል ። የሞት ቅጣት በአጠቃላይ በተለየ ሁኔታ ከባድ ተብለው በሚገመቱ ወንጀሎች ላይ ሲፈጸም ቆይቷል ። ኅብረተሰብ እነዚህ ወንጀለኞች ሊረዱና ሊመለሱ ከሚችሉበት ገደብ ያለፉ ናቸው ብሎ በማሰብና እራሱን በማሳመን እነርሱን የሚያጠፋበትን አሰቃቂ ዘዴ ሲጠቀም ቆይቷል ። በጥንታዊ አውሮፓ ልማድ የሞት ቅጣት በካራ ፣ በፋስ ፣ በጐራዴ ጭንቅላትን ከሳንቃ ላይ በመፈጥፈጥ ወይም በማረሻ በመቁረጥ ፣ አንድን ሰው ከነሕይወቱ በመቅበር ፣ በርሃብ እንዲሰቃይ እንዲሞት ጉድጓድ ውስጥ በመጣል ወይም እራሱን በመቸንከር ውሀ በመድፈቅና ደም በብዛት ፈሶ እንዲሞት በማቁሰል ፣ በመሬት ላይ በመጐተትና አካልን በመሰነጣጠቅ ፣ ከአንድ ተሽከርካሪ ወይም መንኰራኩር ላይ አድርጐ በማሰቃየት ፣ በጋለ ወረንጦ (መቆንጠጫ) በማሰቃየት ቆዳን ገፎ የጎን አጥንትን በመቆራረጥ አካልን በሙሉ በመበጣጠስ ፣ ብረት ላይ ወይም እንጨት ላይ አጋድሞ በመጋዝ በመቁረጥ ከግንድ ላይ አስሮ በማቃጠልና በብዙ ሌሎችም አስከፊ መንገዶች ይፈጸም እንደነበረ አንድ ጽሁፍ ይገልጻል[28]። በዘመናችን ያሉና የሞት ቅጣትን የያዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችና ድንጋጌዎች የሞት ቅጣት አስፈላጊ ካልሆኑ ጭካኔዎች ነጻ በሆነ መንገድ መፈጸም እንዳለበት እስከ መደንገግ ድረስ ተሻሽለዋል ። የ1949 የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሩ ምሳሌ ነው ። የሞት ቅጣትን የያዘው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለቅጣቱ አፈጻጸም ልዩና ግልጽ መመሪያዎች

ይሰጣል ። ቅጣቱ የሚፈጸመው በስቅላት ሲሆን በወታደሮች ላይ ሲሆን ግን በጥይት በመደብደብ እንደሆነ ይገልጻል ። ስለሆነም የሞት ቅጣት ያለአንዳች ጭካኔ ፣ የአካል መቆራረጥ ወይም ሌላ ዓይነት የአካል ጉዳት መፈጸም አለበት ይላል[29]።

የሞት ቅጣት በአጠቃላይ በተለየ ሁኔታ ከባድ ተብለው በሚገመቱ ወንጀሎች ላይ ሲፈጸም መቆየቱን አውስተናል ፣ ሌላው መታወስ ያለበት ነገር ደግሞ የአንድ ወንጀል ከባድነትና አብሮት የሚሄደው ቅጣት በአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን የሥልጣን ቁንጮዎች (የገዥ መደቦች) ወግና ልማድ ወይም ጥቅም የሚያንጸባርቁ አንጸባራቂ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው ። አንድ ምሳሌ ብንጠቅስ በድሮ ጊዜ በእንግሊዝ አገር በስቅላት የሚያስቀጡ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ የወንጀል ዝርዝሮች እንደነበሩ ነው ። ከነዚህም መካከል ጥንቸል መግደል መሐረብ መስረቅ እንጀሪ ዛፍ መቁረጥ ያለፈቃድ አሳ ማስገር ይገኙበት ነበር[30]። ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ የነበረው ግምት የመሬት ከበርቴ ዎች የባለሀብትነት መብት ፍጹም ስለነበርና ጥብቅ በሆነ መንገድ በመደብ በተከፋፈለ ፊውዳላዊ ኅብረተሰብ ይህ መብት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነበርና ነው ። በመሆኑም ፊውዳላዊ ኅብረተሰብ ዛሬ ቀላል የደንብ መተላለፍ በምንላቸው ወንጀሎች ላይ እንኳ ሳይቀር የሞት ቅጣት በመፈጸም ጥቅሙን ያስከብር ነበር (በሌላ በኩል ደግሞ የሃየኛው ምዕተ ዓመት ብሪታንያ የሞት ቅጣትን አስወግዳለች ።)

እ.ኤ.አ. በ1962 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት በሞት ቅጣት ላይ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ከተጠኑት ከአንድ መቶ በላይ ከሆኑ ሀገሮች 35ቱ በሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች የሞት ቅጣትን በግልጽ ሲያስቀሩ ዘጠኙ ደግሞ በተግባር ትተውታል ፣ አብዛኛዎቹ ግን በሕጋቸው ውስጥ አስገብተውት ይገኛሉ ።

(የሞት ቅጣትን በሕግ ጨርሶ ማስቀረት የተጀመረው 1786 ዓ.ም. የቱስካኒው ዳግማዊ ሌዎፖልድ በሙሁሩ በቤካሪያ አነሳሽነት የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ሕግ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው ። የአውስትሪያው ዳግማዊ ዮሴፍ ደግሞ በ1787 ባወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሞት ቅጣትን አስቀርቷል[31]።)

አንዳንድ ኅብረተሰቦች ቀደም ብለው ማለትም በ18ኛው ምዕተ ዓመት የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ምን እንዳነሳሳቸው ሌሎች ግን እስከ አለንበት ዘመን 20ኛው ምዕተ ዓመት ይዘውት እንዲቆዩ ምን እንዳደረጋቸው ማሰብና መመራመር አስቸጋሪ ጥያቄን ያስነሳል ። ይህ ጥያቄ እጅግ በጣም የተወሳሰበ ቢሆንም ቢያንስ በዘመናችን የሞት ቅጣትን መያዝ ጥቅምና ጉዳት በማመልከት ረገድ የሚነሱትን ጥያቄዎች (ነጥቦች) መመርመር ይቻላል ።

ጂን ግራቬን የ1949ኙ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አርቃቂ የሞት ቅጣት በሕጉ ውስጥ የገባበትን ምክንያት በመግለጽ ሲጽፉ «. በኢትዮጵያ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ የሞት ቅጣትን ማስቀረት የማይታለፍ ከመሆኑም በላይ የማይቻልም ነው ። የሞት ቅጣት አስፈላጊነት ለማህበራዊ ደህንነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የፍትሕና የስርዓት ጥልቅ ስሜት በርሱ ላይ የመተመሠረተ ነው ። የፈጣሪ ታላቅ ፍጥረት የሆነው የሰው ሕይወት መጥፋት ሊካስ የሚችለው በጥፋተኛው ሕይወት መስዋዕትነት ብቻ ነው ። እንደመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ ክርስቲያኖች ዕምነት ሞት ሁልጊዜ ለኃጢአተኛው ምሕረትና ስርየት አስፈላጊ

የሆነ ሁኔታ ነው ። በተጨማሪም ለፈጸመው እርኩስ ተግባር መፋቅ አስፈላጊ ነው ። ይህ በሁሉም ዘንድ በተለይም በወንጀለኛው ተቀባይነት ያለውና የታመነ ነው ። የሞት ቅጣቱም የሚፈፀመው ቀደም ሲል ከገለጽነው በፋስና አንገት መቁረጫ ከሚፈጸመው ለየት ባለ ግርማ ሞገስ ባለው ሁኔታ ነው ። » ብለዋል[32]።

የሞት ቅጣት ከሰው መግደል ወንጀል አኳያ በመመልከት አንድ ዘገባ «ሰው መግደል አሰቃቂ እንደሆነ ሁሉ የሞት ቅጣትም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው» ሲል ገልጿል ። ምክንያቱም ሰው መግደል ይህ ነው በማይባል ሁኔታ እጅግ በጣም ለመልካም ምግባር ተቃራኒ የሆነ ጥፋት ስለሆነ ሕብረተሰብ በዚህ ወንጀል ላይ ያለውን ከፍተኛ ቁጣ ለወደፊቱ ወንጀለኞች ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች በጥንካሬ ለመግለጽ እንዲችል ቅጣቱም በዚሁ መጠን ከባድና ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ። በሌላ አነጋገር የሚፈጸመው ቅጣት አግባብ ባልሆነ መንገድ መቀነስ ወይም ማሳነስ ነፍሰ ገዳዩና ሌሎች መሰሎቹ ኅብረተሰባችንን የሰው መግ ደልን ወንጀል አሰቃቂ ነው ብሎ አያምንበትም ወደሚል መንገድ ሊመራው ይች ላል[33]። ከዚህ ላይ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ከላይ የተጠቀሰው የሞት ቅጣት ለምን መኖር እንዳለበት የሚያስረዳው ምክንያት በአንድ ወንጀል እርሱም በሰው መግ ደል ወንጀል ብቻ የተወሰነ ነው ። ከዚህ ለመረዳት የምንችለው የሞት ቅጣት ነፍስ ግድያ ባልሆኑ ወንጀሎች ላይ የሚፈጸምበትን አጥጋቢ ምክንያት ለመግለጽ ጨርሶ አይቻልም ባይባልም ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ነው ።

ስለሞት ቅጣት መቅረት ከሚሰነዘሩት ሃሳቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ባለው ዘገባ ተመልክተዋል ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው

<u>አንደኛ</u> ፣ የመንግሥት ወኪሎች የሞት ቅጣትን በሚፈጽሙበት ጊዜ ሊያ ስወግዱት የማይችሉት ከፍተኛ አመጽ በተቀጭው ግለሰብ ላይ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ይፈጽማሉ ። የዚህ ዓይነቱ ተግባር ለኅብረተሰቡ ደህንነት ሲባል የሚወ ሰድ አስፈላጊ ዕርምጃ ነው ብሎ ማመን መቻሉና በሌላ ዘዴ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልም ብሎ መወሰኑ አጠራጣሪ ነው ።

<u>ሁለተኛ</u> ፣ የሞት ቅጣት መኖር በወንጀል የፍትሕ አስተዳደር ላይ ጉጂ ተጽዕኖ ይኖረዋል ። ወንጀለኛው ተከሶ ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ ሕይወቱ በአ ስጊ ሁኔታ ላይ መገኘት ብቻ በኅብረተሰቡ ዘንድ ጥፋተኛው የተከሰሰበትን ወን ጀል በመርሳት የርሕራሔ የድጋፍ ስሜት እንዲቀሰቀስ ያደርጋል ። ሕግንና የሕ ግን ተፈጻሚነት መደገፍ የሚገባው የሕዝብ ስሜት በዚህ የሞት ቅጣት እስከሚ ፈጸምበት ጊዜ ድረስ በሚከናወነው አስከፊ ሁኔታ የተነሳ ወደ ሌላ አቅጣጫ ያመራል ።

<u>ሶስተኛ</u> ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ለማስፈጸም በሚደረገው ጥረት አንዳ ንድ የተሳሳተ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች መስጠታቸው አይቀርም ። አንዳንዴም ብዙ ጊዜ ካለፈ በኋላ ካልሆነ በቀር ስህተቱን ለማግኘት አይችልም ። እንደዚህ ያሉ ስህተቶች የሞት ቅጣቱ ከተፈጸመ በኋላ ሊታረሙ አይቻልም ። እንደዚህ ያለ ሁኔታም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተገነባበትን ዓላማና መልካም ምግባር ጨርሶ ያናጋዋል ።

<u>አራተኛ</u> ፣ ልምድ እንደሚያሳየው የሞት ቅጣት በጣም መጠነኛ በሆነ እኩ ልነት እንኳ አይፈጸምም ።

አምስተኛ ፡ የሞት ስጋት ከረጅም ጊዜ እስራት ስጋት የበለጠ የማስጠንቀቂያነት ፍቱንነት ይኑረው አይኑረው የዘረዘርናቸው አስተያየቶች የሞት ቅጣት መቅረትን እንድንመርጥ ያደርጉናል ። በእርግጥ የሞት ቅጣት በማስጠንቀቂያነት የጠቀመበት የተለዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። ሆኖም የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ይህ ሁኔታ በመጠን በኩል ይህን ያህል ትኩረት የሚሰጠው አይደለም[34]።

እንግዲያውም ከላይ የገለጽነው ሁሉ የቅጣት ታሪክ በቅጣት ከባድነትና በወንጀል መፈጸም መካከል ያለውን ዝምድና እያሳይም በሚለው ስለሞት ቅጣት መቅረት በሚከራከሩ ሰዎች አባባል ሊደመደም ይችላል ፣ የተወሳሰበው የወንጀል መንስኤ ለሚመረምር ሰው ይህ አባባል ግልጽ ነው ። አንድ የእንግሊዝ የቅጣት ታሪክ እንደሚያስታውሰን ታይበርን በተባለ ቦታ ኪስ አውላቂዎች በአደባባይ በስቅላት ሲቀጡ ሕዝብ ተሰብስቦ ቅጣቱን በመመልከት ላይ እንዳለ ሌሎች ሰዎች ኪስ ሲያወልቁ ተይዘዋል[35]።

አንድ ሰው ኅብረተሰብ በሞት ቅጣት ምን ግብ ይመታል ብሎ ሊጠይቅ ይችላል ። ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ከባድ አይደለም ። የሞት ቅጣትና እርሱን ተከትሎ የሚመጣው ጭካኔ ለኅብረተሰብ ከፍተኛ የበቀል ዕርምጃ ሆኖ አገልግሏል ። ይህ ሊካድ አይችልም ። ነገር ግን በቀል ኅብረተሰብ የሚያፍርበት እንጂ የሚያኮራው የቅጣት ግብ አይደለም ። በቀል የአውሬነት (የአለመሰልጠን) ምልክት በመሆኑ በበቀል አንጻር ብቻ የሞትን ቅጣት ብንመለከት መቅረቱ መደገፍ ያለበት ጉዳይ ሆኖ ይቀርባል ።

የሚቀጥለው የቅጣት ግብ ይኸውም እርማት ከዚህ ላይ ፈጽሞ ሊነሳ አይችልም።ምክንያቱም ኅብረተሰብ በሞት ቅጣት በመጠቀም እንዲህ ያለ ሰው ሊታረም አይችልም የሚል ውሳኔ በመስጠቱ ነው ። በትክክል ወይም ሳይገባው ኅብረተሰብ የማረም ችሎታው ዝቅተኛ እንደሆነ ተቀብሏል ። በተጨማሪ እንዲህ ያለ ወንጀለኛ ለኅብረተሰቡ ከእንግዲህ ወዲህ አይጠቅምም ከሚል ውሳኔ ላይ ደርሷል ። እነዚህም ለመወሰን አስቸጋሪ የሆን ሁኔታዎች ናቸው ። ያም ሆነ ይህ ኅብረሰብ በአንድ ግለሰብ ላይ የሞት ቅጣት ሲፈርድ የሚወስነው ይህንኑ ነው ።

ከሞት ቅጣት አኳያ በመጨረሻ የምንመለከተው የቅጣት ግብ ማስጠንቀቂያነት ነው ። የሞት ቅጣት በማስጠንቀቂያነት ምን ያህል ያገለግላል የሞት ቅጣት የተፈጸመበት ወንጀለኛ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይደግም ወይም ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም ፈጽሞ ችሎታ አጥቷል ። ስለዚህም የሞት ቅጣት ከግለሰብ ማስጠንቀቂያነት አንጻር ምንም ዓይነት አስጠንቃቂ አይደለም ። የግለሰባዊ ማስጠንቀቅ ግብ የሚያተኩረው ወንጀለኛውን በሚጣልበት ማህበራዊ ቅጣት አማካይነት ወንጀልን እንደገና መፈጸም ጠቃሚ እንዳልሆነ በማስተማር ላይ ነው ። ይሁን እንጂ የሞት ቅጣት ወንጀለኛው ካለፈው ስህተቱ ተምሮ መልካም ዜጋ እንዲሆን ምንም የሚያበረክተው ትምህርት የለም ። የሞት ቅጣት ወንጀለኛው ለዘለቄታቸው በኅብረሰቡ ላይ ወንጀል እንዳይፈጸም ቢያደርገውም ኅብረተሰቡ ይህን ያደረገው ወንጀለኛው በቅጣት አማካይነት በማስተማር ሳይሆን እንዲሁ ወንጀለኛውን ለዘለዓለሙ በማስወገድ ነው ።

ታዲያ የሞት ቅጣት መቅረት እንዳለበትና እንደሌለበት የሚወስነው ባለው አጠቃላይ የማስጠንቀቂያነት ዋጋ ነው ። የሞት ቅጣት ለወደፊቱ ወንጀለኞች ሊሆኑ የሚችሉትንና ኅብረተሰቡን በጠቅላላው የወንጀል ውጤቱ መራራ መሆኑን

በማስታወቅ እነዚህ ለወደፊቱ ወንጀለኛ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ወንጀል እንዳይ ፈጽሙ የማስጠንቀቂያነት ትምህርት ይሰጣል ? ይህ እንዲሁ ልብ ወለድ መልስ የሚሰጠው ሳይሆን በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ መልስ የሚያስፈልገው ቁምነገር የተሞላው ጥያቄ ነው ።

አንድን የሞት ቅጣት ከነፍስ ግድያ ወንጀል ጋር አጣምሮ የመረመረ ጥናት ደራሲ ሲያጠቃልል «. የሞት ቅጣት ስጋት (ፍራት) ለወደፊቱ ወንጀል ከመ ሥራት እንዲቆጠብ በሰው ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ ካለው ፍርሃት ከፍ ባለ ቁጥር በዚሁ መጠን ፍቱን ይሆናል ብለን መገመት እንችል ይሆናል ። የሞት ቅጣት የማስጠቃት ወይም የመከላከል ተጽዕኖ ካለው የሚከተሉት የመላ ምት አባባሎች ትክክል ይሆናሉ ብሎ መገመት ትክክለኛ ይመስላል ።

ሀ/ ሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ እኩል ሆነው የነፍስ ግድያ ወንጀሎች የሞት ቅጣትን ካስቀሩ ሀገሮች ይልቅ የሞት ቅጣትን በሥራ ላይ ካዋሉ ሀገሮች ያነሱ መሆን አለባቸው ።

ለ/ የሞት ቅጣት ሲቀር የነፍስ ግድያ ወንጀለኛ መጨመር አለባቸው ። እንደ ገና ከሥራ ላይ ሲውል ደግሞ መቀነስ አለባቸው ።

ሐ/ የሞት ቅጣት በሚፈጸምባቸው ማኅበረሰቦች የማስጠንቀቂያነት ኃይሉ ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል ፤ ከዚህም በላይ በነፍስ ግድያ ወንጀሎች ቁጥር ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይገባል ።

የተመረመሩት ማስረጃዎች የሚከተለውን ያሳያሉ ።

1. በነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያት የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር በተለያዩ አገሮች ቡድን አንድ ዓይነት አይደለም ።
2. በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የሚገኙ አገሮች ተመሳሳይ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥርዓት እያላቸው እኩል የሕዝብ ቁጥር እያላቸው የሞት ቅጣትን ያስቀሩ ትንና ያላስቀሩትን መለየት አይቻልም ።
3. በነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያት የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር የሞት ቅጣትን ባስ ቀሩም ሆነ ባላስቀሩ አገሮች ተመሳሳይ ነው ።

ከዚህ ሊከተል የሚችለው ማስጠንቀቂያ እንዳየነው ሁሉ የሞት ቅጣት ለነፍስ ግድያ ወንጀል በሚሞቱት ሰዎች ቁጥር ላይ ጉልቶ የሚታይ ተጽዕኖ የለውም[36]።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከተው የተባበሩት መንግሥታት ዘገባ በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በአሁኑ ጊዜ በአንጻራዊ አስተያየት በርካታ እንደሆኑ የገለጸው የወንጀሎችን አይነትም በመተማመን እንደሚከተለው ያብራራል ።

ከነፍስ ግድያ ሌላ ሌሎች ወንጀሎችን በሞት የሚቀጡ አገሮች ቁጥር እየ ቀነሰ ነው በማለት ያጠቃልላል ። ይሁን እንጂ ዘገባው ያለፉት ሠላሳ ዓመታት ሶስዩሎጂካዊ የሕግ ዋና ዋና ባሕርያት ብሎ በሚጠራው ሁኔታ የታጀበ ነው ። ይኸውም የሞት ቅጣት ከፖለቲካ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን እንደገና መታ የቱ ነው ። ዘገባው እንደሚሰነዝረው ኃሳብ ለዚህ ሁኔታ ኃላፊው ወይም መንስ ኤው ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለማውጣት የሚደረገው አዝማ ሚያ ነው ። ይህ የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ ለመጀመሪያው የ20ኛ ምዕተ

ዓመት ግማሽ የሞት ቅጣትን ለማጥፋት ይደረግ የነበረውን ዓለማቀፋዊ አዝጋሚ ጉዞ ገታው ። እንዲሁም ይህ ሁኔታ የሞት ቅጣት በቀረባቸው ሀገሮች እንደገና እንዲታይ ከማድረጉም በላይ በሌሎች አገሮች ደግሞ ተፈጻሚነቱ በብዙ ወንጀሎች ላይ እንዲስፋፋ አድርጓል[37]።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የሞት ቅጣት ከፖለቲካ ወንጀሎች ጋር እየተያያዘ መጥቷል ። አንድ አፍሪካዊ ጸሐፊ ስለጉዳዩ ሲገልጽ የአፍሪካ አስከፊው የነጻነት ገጽታ የሞት ቅጣት ለብዙ የፖለቲካ ወንጀሎች በቀላሉና በሠፊው መልስ ሆኖ መቅረብ ነው ብሏል[38]። እንዳጋጣሚ ይህ በተለይ የአፍሪካ ባሕርይ ብቻ ሳይሆንም በመላው ዓለም የተለመደ ነው[39]።

ይህን ክፍል ለመደምደም የሞት ቅጣት በሁሉም ሕብረተሰቦች ዘንድ በሥራ ላይ ውሏል በማለት ለማጠቃለል ይቻላል ። ሆኖም ሀያኛው ምዕተ ዓመት ለሞት ቅጣት መፈጸም ገደብ ተደርጐበታል ። በእርግጥም ብዙ አገሮች በሕጐቻቸው የሞት ቅጣት እንዲቀር አድርገዋል ። ሌሎች ደግሞ የሞት ቅጣት በሕጐቻቸው ውስጥ እንዲቆይ ቢያደርጉም በግፍ አገዳደል ወንጀል ላይ ብቻ ተፈጻሚነት እንዲኖረው አድርገዋል ። በመሆኑም የሞት ቅጣት አግባብ ነው ከተባለ የሚፈጸመው በተለይ በነፍስ ግድያ ወንጀል ላይ ይሆናል ። የሚያስገርመው ግን በዚህ ምዕተ ዓመት ቅጣት ተፈጻሚነት በተለያዩ የፖለቲካ ወንጀሎች በርክቶ መታየት ነው ። የሞት ቅጣትን የነፍስ ግድያ ላልሆኑ ወንጀሎች በተለይም በፖለቲካ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ገለልተኛ ከሆነ ምሁራዊ አመለካከት አንጻር ሲታይ አግባባዊነቱና ትክክለኛነቱ በሠፊው ጥናት የሚያስፈልግ ሆኖ ይገኛል ።

## IV ወደ ሳይንሳዊ የቅጣት አቀጣጫ

በዚህ ሥራ በሶስተኛው ክፍል ሶስት ባሕላዊ የቅጣት ዓይነቶች ተወስደው ሲገመገሙ አጥጋቢ ሳይሆኑ ቀርተዋል ። ይህም የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ያስነሳል ። የጥቂት ባሕላዊ ቅጣቶችን አስፈላጊነት ስላቃለልን ታዲያ ሕብረተሰብ ቅጣትን ጽንሰ ሀሳብ ጨርሶ ማስወገድ አለበት ማለት ነው?

ኅብረተሰብ የተመሠረተበትን ወግ በሚጥሉ አፈንጋጮች ላይ ቅጣት ወይም አራሚ እርምጃ መውሰድ ለኅብረተሰቡ ዘላቂ ሕልውና አስፈላጊ ነው ። እንደዚህ ያሉ አራሚ እርምጃዎች ከሌሉ የኅብረተሰቡ አቋም ይናጋል ፤ ከአረመኔያዊነትና ከሕግ አልባነት ገደል ውስጥ እንወድቃለን የሚለው ፍራቻም አሳሳቢ ነው ። ነገር ግን ቁምነገረኛው ጥያቄ ታዲያ ቅጣት በምን ዓይነት መኖር አለበት? የሚለው ነው ። በዚህ ጥያቄ አኳያ ነው የባሕላዊ ቅጣቶች ዋጋ (ጉዳትና ጥቅም) የተነሳው ። አንድ ልንሰነዝረው የምንወደው ቀላል ሀሳብ ቅጣት መበቀያ መሆን እንደሌለበት ነው ። የበቀል ቅጣት ኅብረተሰብንም ሆነ አፈንጋጩን የማይጠቅም ጐጂ ኃይል በመሆኑ መሠረታዊውን የቅጣትን ዓላማ የሚጻረር ይሆናል ። ቅጣቱ አስጠንቃቂ ወይም አራሚ መሆን ነው ያለበት ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ኅብረተሰብ በፈጠራ ችሎታው በመጠቀምና ምንጊዜም በመዳበር ላይ ባለው የሳይንሳዊ ሥነ ባሕርይ ጥበብ በመረዳት የተሻሉ የማረሚያ ቅጣቶች የመፍጠር ግዴታ አለበት ። ቅጣት ከታረሙና ወደ ኅብረተሰቡ ከተመለሱ ዜጐች አኳያ ሲታይ ፍጹም እንኳ ሳይሆን በመጠኑም ቢሆን የሚገኘው መልካም ውጤት ከፍ እንዲል የሚያደርግ ጥሩ ሙከራ (ኤክስፐርሚንት) ነው ። ይህን የወንጀልን ችግር ለመዋጋት ኅብረተሰቡ አስተዋይነትና ብልህነት የተሞላበት ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት ። በዚህ አስፈላጊ ጉዳይ ላይ ሀሳብ የሚያመነጩ ሁሉ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ሲባል መበረታታት ይኖርባቸዋል ።

በመሆኑም ኅብረተሰብ የትኛው ዓይነት ቅጣት ነው አስጠንቃቂና አራሚ ብሎም ተስፋ ሰጪ የሚሆነው የሚለውን ትክክለኛ ጥያቄ ሊያተኩርበትና መፍትሄ ሊፈልግለት ይገባል ። በቅጣት ጥያቄ ላይ ሥር ነቀል አመለካከት መልካም ተቀባይነት ሊኖረው ቢችልም ብዙ ሕብረተሰቦች ባሕላዊው የቅጣት ዓይነት ወደ ተሻለና ሳይንሳዊ የቅጣት ዓይነት ለመለወጥ አዝጋሚ የለውጥ መንገድ የሚከተሉ ነው የሚመስሉ ። የአዝጋሚ ለውጥን መንገድ እንዲከተሉ የሚያስገድዷቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ዋናው ምክንያት የሁሉም ኅብረተሰቦች ባሕርይ በአብነት ሊጠቀስና ሊታይ የሚችል የዘመናዊ ቅጣት ንድፍ (ዕቅድ) ያለመኖሩ ነው ። የእንደዚህ ዓይነቱ ዕቅድ ያለመኖር እንደዚህ ያለውን አሳሳቢና ቋሚ ማኅበራዊ ችግር ኅብረተሰብ በግድ የለሽነት እንደተመለከተው የሚያመለክት ነው ። በመጨረሻ ኅብረተሰብ በችግሩ ላይ እንዲያተኩር በሚገደድበት ጊዜ በየዕለቱ የሚያደርገውን ሙከራ መሠረት በማድረግ ብቻ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ እቅድ በማውጣት መሥራት ይኖርበታል ። እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት እንደዚህ ያለው ሙከራና እቅድ የሰው ኃይል ማሰማራትና ገንዘብ መመደብ ከመጠየቁም ሌላ ውጤት ለማግኘት ንቁ ጥረት ይጠይቃል ። የመጨረሻው ለውጥ ቀላልና የማይጨበጥ አይሆንም ነገር ግን እውነተኛው ለውጥ በአፈንጋጩና በኅብረተሰቡ አስተሳሰብ አድማስ ላይ ይሆናል ። እርግጥ የድሮዎቹ የአካል መቆራረጫ መሣሪያዎች ወደ ቤተመዘክር እንደገቡ ሁሉ የአሁኖቹ በሽቦ የታጠሩና የሚጠብቁ እሥር ቤቶችም ጊዜ ያልፍባቸዋል ። በቦታው ልዩ ዓይነት ከእሥር ቤት የተሻሉ የሕክምና ማዕከላት የሚመስሉ ተቋሞች ሊያብቡ እንደሚችሉ ይጠበቃል ።

በአንዳንድ አገሮች በአሁኑ ጊዜ በሙከራ ላይ ያለው እርማት ፍርድን ግለሰባዊ ማድረግ ነው ። በብዙ አገሮች ሕጋዊው የመንግሥት አካል ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ መስጠት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ወንጀሎች ቅጣቱን ይወስናል ። በብዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች ቅጣት በመወሰን በኩል የሕጋዊው ሚና ለተለያዩ ወንጀሎች ከፍተኛና ዝቅተኛ የእሥራት ዘመን ማበጀት ነው ። ከዚህ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ወንጀለኛ ላይ ፍርድ የመስጠቱ ጉዳይ ለዳኛው ከመተውም በላይ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ በአጠቃላይ አነጋገር የመጨረሻ ነው ። ይሁን እንጂ አንድ ሌላ ሀሳብ ፤ ምናልባት «ያልተወሰነ ፍርድ» ሊባል የሚችል በመፍለቅ ላይ ነው[40]። ይህ ማለት ደግሞ በአጠቃላይ መንገድ በሐጋጊው የተደነገገው በመጀመሪያ በፍርድ ቤት በሚታይበት ጊዜ ግለሰባዊ ይሆናል በመሆኑም በአንድ ግለሰብ ወንጀለኛ ላይ ፍርዱን የመወሰን ኃላፊነት ለአይን ቁራኛው ቦርድ በመስጠት ዳኛው ከፍተኛውንና ዝቅተኛውን ፍርድ ብቻ ይወስናል ። እርግጥ የዚህ «ያልተወሰነ ፍርድ» ሌላው መልኩ በዳኛውና በዓይን ቁራኛው ቦርድ መካከል የሥራ ክፍፍል መፍጠር ነው ፤ ይኸውም ዳኛው ጥፋቱን የጥፋቱንም ደረጃ በመወሰን ወንጀለኛው ወደ ዓይን ቁራኛው ቦርድ ያስተላልፈዋል ፤ ቦርዱም ወንጀለኛውን በጥንቃቄ ከተከታተለ በኋላ እርግጠኛውን የቅጣት ጊዜ ይወሰናል ። ያልተወሰነ የፍርድ ኃሳብ ዋናው ባሕርይ ብቁ የሆኑ የዓይን ቁራኛ ቦርዶች ማቋቋምና የእስር ቤት አሠራርን ድጋፍ ሰጭ ከሆኑ ተቋሞች ጋር ማቆየት ነው ።

ሌላው ሥር በመስደድ ላይ ያለው ሙከራ በቀላል ወንጀሎች ላይ የሚጣለውን የአጭር ጊዜ እሥራት በአንዳንድ አገሮች በሁለተኛ ደረጃ ቅጣቶች ተብለው የሚጠሩት የተለያዩ እርምጃዎች መተካት ነው ፤ ከእነሱም መካከል የገንዘብ ቅጣት ፤ ልዩ ሥራ ፤ ጊዜያዊ የመብት ገፈፋ ፤ ማስጠንቀቂያና በገደብ መልቀቅ ይገኙበታል[41] የአጭር ጊዜ እሥራትን በነዚህ እርምጃዎች መተካት ማኅበራዊም ሆነ ኤኮኖሚ

ያዊ ቁም ነገር አለው ። በመጀመሪያ ነገር ወንጀለኛው ከአምራችነት ተግባሩ ተነ ስቶ አይወሰድም ፤ ለእርሱ ዘበኛ ፤ ምግብና መኝታ ሌሎችም ከእሥር ቤት ጋር የሚ ሄዱ ወጭዎችን በማቅረብ ኅብረተሰቡ አይቸገርም ። ሁለተኛ የቅርብ ወዳጆቹና ቤተሰቦቹ በእርሱ መታሰር በተዘዋዋሪ አይሰቃዩም ። ሶስተኛ የሕብረተሰብ የቅ ጣት ግቦች ማለትም ማስጠንቀቅና ማረም ያለምንም እንከን ከሥራ ላይ ይውላሉ ። የትኛው እርምጃ ለየትኛው ወንጀለኛ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ የሚወሰነው በእ ርግጥ ብዙ መለኪያዎችን በመውሰድ እያንዳንዱን ጉዳይ ለብቻው በመመልከት ነው ።

እንደገና ወደ እሥር ቤት አሠራር በመመለስ እንደ ስካንዲነቪያ አገሮች በመሳሰሉ ሥርዓቶች የተገኘው ልምድ መጥቀሱ ጥሩ ይመስለናል[42]። ስለወንጀል በሶሲዮሎጂካል ክሪሚኖሎጂ ዘዴ በማጤን የእሥር ቤቱን አሠራር በዘመናዊ መርሆዎች እንዲመሠረት ገፋፍቶታል ። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ፤

ሀ/ በፖሊሲ አወጣጥ ረገድ ፍጹም የሆነ ማዕከላዊነት

ለ/ የተቋሞች መለያየት

ሐ/ ሊታረሙ የሚገባቸውን ሰዎች ማዕከላዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በየተቋሞች ማሠራጨት ። እንደዚህ ያለው የእሥር ቤቶች አሠራር በማዕከላዊ መንግሥት ደረጃ ፖሊሲ ማውጣት በጥንቃቄና በማስተዋል እቅድ መንደፍን በርካታ የሰለጠነ የሰው ኃይል በተለያየ ሥራና ሙያ የሚያተኩሩ ብዙ የእሥር ቤት ክፍሎችና ከፍተኛ ባጀት ማስፈለጉ አያጠራጥርም ። የእሥር ቤትን አሠራር ተከትሎ የሚመጣው የልማደኛ ወንጀለኛነት በከፍተኛ ሁኔታ ተደጋግሞ መታየት የመልካም ውጤት ሳይሆን የውድቀት ምልክት መሆኑ ግልጽ ነው ። ከጠቅላላው የውድቀት አዝማሚያ ለየት ባለ ሁኔታ ከዚያም የሚታዩት አንዳንድ የመልካም ውጤት ምልክቶችም የተሀድሶና የፈጠራ ውጤት መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል ። በርካታና በደህና ሁኔታ ከታጠቁ ዘበኞች ይልቅ የአእምሮ ሐኪሞችን የሥነ አዕ ምሮ ሊቃውንትን የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ሠራተኞችን የማኅበራዊ ኑሮ ሊቃ ውንትን የሃይማኖት ሰዎችንና የሕግ ባለሙያዎችን በሥራ ማሠማራት ከጨለማና ጠባብ ቤቶች ይልቅ እሥረኞች አገልግሎት የሚያበረክቱባቸውን ሠፋፊ እርሻዎች ማስፋፋት ፤ ቀስ በቀስ እሥረኞችን ከሕብረተሰቡ ጋር ለማስተዋወቅ የተመላላሽ እሥር ቤቶችን ማቋቋም ፤ ሰብዓዊና አስተዋይ የሆኑ አመለካከቶች እንዲስፋፉ ማድረግ ፤ ለምሳሌ የፈጠራ ወይም ምርታማ የሆኑ ሥራዎች እንዲስፋፉ ማድረግ ፤ እንዲሁም ከቤተሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠንከርና በእሥር ቤት የትምህርት መስፋፋት ፤ እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎችን ማሻሻል ይህ ሁሉ እሥረኞችን ኅብረተሰብ እንደጭራቅ ሳይሆን እንደሰው ፤ ጥቅም እንደሌላቸው ሳይሆን ጥቅም እንደሚሰጡ አድርጐ እንዲመለከታቸው ያደርጋል ። እነዚህ ድጋፍ ሰጭ ተቋሞች ናቸው በእሥር ቤት አሠራር መልካም ውጤት እንዲታይ ሊያደርጉ የሚችሉ[43]። የእሥር ቤትን ቋሚ ሕልውና በሚቃወሙ ወይም አሁን ከምናውቀው ለየት ያለ የእሥር ቤት ዓይነት እንዲኖር በሚመርጡ ሰዎች ተደ ጋፊነት ሊኖረው የሚገባ ሀሳብ ይሠነዘራል ። ይኸውም እሥራት እንደ ሕክምና መታየት አለበት የሚል ነው ። እንደዚህ ያለው ሕክምና ፍቱን እንዲሆን ካስፈ ለገ በፈቃደኛነት ላይ መመሥረት ይኖርበት ይሆናል የሚሉም አሉ ፤ ምክንያቱም አለ ወንጀለኛው ትብብር ሊፈወስ አይችልምና ነው ። በመሆኑም እሥራት ወን ጀለኛው ራሱ ሊመርጠው የሚችል አማራጭ የሕክምና ዓይነት ሆኖ ሊቀርብ ይች ላል[44]።

የቅጣት አኳያ ከልማደኛ ወንጀለኛነትና ከወንጀል መስፋፋት አዘቅት ለመውጣት ያለው ብቸኛ መንገድ በሥነ ባሕርይ ሳይንሶች ውስጥ ከላይ የጠቀስናቸው ፍሬያማ ሀሳቦች ሥር እንዲሰዱ ማድረግ ይመስላል ። ይሁን እንጂ አብዛኛው ምርምርና ጥረት የሚያተኩረው አፈንጋጮችን በማረም በኩል ሳይሆን በመከላከል በኩል ነው ። ወንጀልን ለመዋጋት መጀመር ያለበት ከቅጣት ሳይሆን ዋና ዋና የወንጀል መንስኤዎችን ለይቶ በመረዳት ሕብረተሰብን እንደገና በመዋቅርና እንደአስፈላጊነቱ አቋሙን በማጠናከር መሆን አለበት[45]።

## V <u>ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ</u>

ፍትሕ መሠረታዊ ብቻ አይደለም ፤ ሥነ ሥርዓታዊም ጭምር ነው ። ፍትሕ የሚመለከተው የገበሬውን ላም የሰረቀውን ሌባ ምን እንደምናደርገው ብቻ ሳይሆን የምናደርገውን ነገር እንዴት እንደምናደርገው ጭምር ነው ። በተጨማሪ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አስፈላጊነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ አይደለም ፤ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ሳይኖር መሠረታዊ ፍትሕ ሊሰጥ አይችልምና ።

አንድ ሕብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ የፈጠራ ችሎታ እንዳለውና ተራማጅ መሆኑና አለመሆኑ አንድን አፈንጋጭ ለመቅጣት በሚደረገው ሂደት ፍትሕን ለማግኘት ለነዚህ መሠረታዊ ሥነ ሥርዓቶች ባለው ታማኝነት በድጋሚ ይንጸባረቃል ። መሠረታዊ የሆኑት የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች በቀላሉ ሊጠቃለሉ ይችላሉ ። ቀላል መስለው ሊታዩ ቢችሉም ለፍትሕ መገኘት የእነርሱ ተፈጻሚነት ፍጹም አስፈላጊ ነው[46]።

ከነዚህ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች <u>የመጀመሪያው</u> «የሕግነት መሠረት» በመባል የሚታወቀው መርህ ነው[47]። ይህም ማለት መፈጸም የማይገባው ድርጊት ከመፈጸሙ መደረግ የሚገባው ነገር ካለመደረጉ አስቀድሞ ድርጊቱ ወንጀል እንደሆነ በሕግ መመልከት አለበት ። በሕግነት መሠረት መርህ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ሌላው ነገር ደግሞ የአንድ ወንጀል ክብደትና ክብደቱን የሚያንጸባርቀው በወንጀሉ ላይ የተጣለው ቅጣት ነው ። ከመፈጸሙ አስቀድሞ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ባልተነገረ ድርጊት ላይ ተመስርቶ በአንድ ግለሰብ ላይ ክስ ማቅረብ ተገቢ አይሆንም ፤ በመሆኑም የሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ ተቃራኒ ይሆናል ።

<u>ሁለተኛው</u> የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል«የንጽህና ግምት»የሚባለው ነው[48]። አንድ ወንጀል ተፈጽሞ አንድ ሰው በጥርጣሬ በሚያዝበት ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ እስከሚገኝ ድረስ ንጹሕ እንደሆነ መቆጠር አለበት ፤ ወንጀሉን የፈጸመው እርሱ ሊሆን ወይም ላይሆን ስለሚችል ነው ። አንድ ግለሰብ እንደወንጀለኛ ከመቆጠሩ በፊት ወንጀለኛው እርሱ ለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል ። አስቀድሞ አንድን ግለሰብ እንደወንጀለኛ መቁጠርና የወንጀለኛ አያያዝ እንዲደረግለት ማድረግ በኋላ ወንጀለኛ እንዳልሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ተገቢ አይሆንም ። ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ከአንድ ወንጀል መፈጸም ወንጀለኛውን ለይቶ እስከ ማወቅና ቅጣቱን እስከመወሰን በሚደረገው ሂደት ትዕግሥትንና እርግጠኛነትን ይጠይቃል ግለሰቡ ወንጀለኛ ለመሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት አቃቤ ሕጉ ነው[49]። ግለሰቡ ወንጀለኛ ለመሆኑ አቃቤ ሕጉ ሸንጎውን ማሳመን አለበት ። ሁሉም ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የአንድ ግለሰብ ጥፋተኛነት በበቂ ማስረጃ ሳይረጋገጥ ሲቀር ግለሰቡ እንደንጹሕ ተቆጥሮ በነፃ መለቀቅ አለበት ። «የንጹሕና ግምት» የፍርድ ሥራው ሂደት እስከ ተፈጸመ ድረስ የሚቀጥልና ማስተባበያ እስካልቀረበበት ድረስ ሳይነካ የሚቆይ ነው ።

ሶስተኛው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል ብቁና ገለልተኛ የሆነ ሸንጎ መኖርን ይጠይቃል ። ስለአንድ ግለሰብ ጥፋት ወይም ንጽሕናና ስለሚጣለው ቅጣት ውሳኔ የሚሰጡ ሰዎች በችሎታቸው ብቁ መሆን አለባቸው ። በቀረበው ማስረጃ ብቻ ላይ ከተመሠረተ ብይን ላይ ለመድረስ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉዳዩን በቅን ልቡና ማየት ይኖርባቸዋል ። ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት የሌላቸው ነገሮች ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው አይገባም ። ሸንጎውን ገለልተኛ ለማድረግ በሚሰጠው ገለልተኛ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ነገሮች ፤ ለምሳሌ ከተከሳሽ ጋር አስቀድሞ የነበረ ጠላትነት ፤ ወይም በጉሳና በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ጥላቻ ፤ የሥልጣን ብልግና ወዘተ መጋለጥና መወገድ ይኖርባቸዋል ። በሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ መርሆዎች ውስጥ ያሉትን መብቶች ለመጠበቅ እንደዚህ ያለ ገለልተኛ ሸንጎ ብቻ ነው በቀረበው ማስረጃ ላይ ከተመሠረተ ውሳኔ ላይ ሊደርስ የሚችለው ። በዚህ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል ማለትም የገለልተኛ ሸንጎ መኖር ውስጥ አንድ ሰው የይግባኝን ሀሳብ ሊጨምር ይችላል[50]። ብቁና ገለልተኛ ሸንጎ ቢኖርም እንኳ ሰው ከሰብዓዊ ደካማነት የጠራ ሊሆን ስለማይችል ስህተት የመሥራቱ አደጋ ሊወገድ የማይችል ነው ።

አንድ በበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከሳሽ ገለልተኛና ብቁ ወደሆነ የበላይ ፍርድ ጉዳዩን የመውሰድና ታች የተሠራውን ስህተት ለማሳረም መብት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ስለዚህ በአንድ በአርአያነት ሊወሰድ በሚችል ሥርዓት ውስጥ ያለ የፍርድ ቤቶች መዋቅር ወይም የሥልጣን ተዋረድ አንድ ተከሳሽ ጉዳዩን በይግባኝ በሌላ ገለልተኛና ብቁ በሆነ ፍርድ ቤት እንደገና ለማስወሰን ሊኖረው የሚገባውን መብት መጨመር አለበት ።

አራተኛው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል በአንድ የችሎት አዳራሽ ውስጥ የሚደረገው ተውኔታዊ ሂደትና ከዚህ ጋር የተያያዙትን ሌሎች ነገሮች ይመለከታል ። ተገቢ ምክንያቶች ከሌሉት በስተቀር (ለምሳሌ ፤ የሥነ ምግባር ፤ ንጹህ ለሆኑ ሶስተኛ ወገኖች አግባብ ያልሆነ ነገር ፤ የመንግሥት ጸጥታ ወዘተ) ችሎቱ ለማንኛውም ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ክፍት መሆን አለበት ። «ፍትህ መስጠት ብቻ ሳይሆን ፍትሕ ሲሠራም መታየት አለበት» የሚለው የእንግሊዝኛ አነጋገር ይህንን ያመለክታል ። የክሱ መስማት ያለአንዳች አስፈላጊ የሆነ መጓተት መፈጸም አለበት ፤ ፍትሕን ማዘግየት ፍትሕን መንሳት ነውና ። ተከሳሹ በምን ወንጀል እንደተከሰሰ እንዲሁም የቀረበበት ማስረጃና ማን እንደሚመሰክርበት በማያሻማ ቋንቋ ሊነገረው ይገባል ። ከዚያ በኋላ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ የሚያስችለው በቂ ጊዜና እርዳታም መሰጠት አለበት ። ምስክሮች የመጠየቅና መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት ፤ እንዲሁም የቀረበበትን ማስረጃ የመቃወም መብት ፤ በመጨረሻም የራሱን ማስረጃ (ኤክስፐርትም ሆነ ሌላ) ካስፈለገ በሕብረተሰቡ ኪሳራ ማቅረብ ተከሳሹ ሊኖሩት የሚገቡ መብቶች ናቸው[51]። እነዚህ መብቶች የቱን ያህልና እንዴት መስጠት እንዳለባቸው ዝርዝር ደንብና ሥርዓት ሊያስፈልጋቸው ይችላል ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ያሉ መብቶች መንፈግ ዞሮ ዞሮ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትህን ወደ መንፈግ ያመራል ፤ ይህም ጨርሶ ፍትሕን ወደ መንፈግ ያደርሳል ።

አምስተኛውና የመጨረሻው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ አካል ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነው ። ቅጣት ምንጊዜም ቢሆን ግለሰባዊ መሆን አለበት ፤ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ብቻ ቅጣቱን መሸከም አለበት ። በወንጀለኛው ጥፋት ማሕበረሰቡን ፤ ዘመዶቹን ወይም ጐረቤቶች በመሆናቸው ብቻ መቅጣት ከፍትሕ መሠ

ረታዊ መርሆዎች ጋር አብሮ አይሄድም[52]። ከዚህም ሌላ ግለሰባዊ ቅጣት በቂ መሆን አለበት ፤ ሆኖም አስፈላጊ ባልሆነ መንገድ መደጋገም የለበትም ። ድጋሚ ቅጣት መወገድ ያለበት ተግባር ነው[53]።

አንድ ወንጀለኛ ቅጣቱን ከፈጸመና ወደ ሕብረተሰቡ ከተመለሰ ቅጣቱ ወንጀሉን ይፍቅለታል እንጂ ወንጀሉ በሄደበት ቦታ ሁሉ እንደ ጥላ አይከተለውም ። ወደ ሕብረተሰቡ የተመለሰው ወንጀለኛ በሕብረተሰብ አንድ ሌላ እድል ስለተ ሰጠው እንደማንኛውም የሕብረተሰቡ አባል ይታያል ። ቅጣቱ የበለጠ ሳይንሳዊ በሆነ ቁጥር አፈንጋጩም ፍጹም ወደ ሕብረተሰቡ ይመለሳል ፤ እንደዚህ በሙሆኑም ድጋሚ ወይም የማያቋርጥ ቅጣት ምንም ዓይነት ገንቢ አገልግሎት አይኖረውም

በዘመናዊ ሕጐች ውስጥ እነዚህ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች አንድ በአንድ ተብራርተው ይገኛሉ ። በአፈጻጸማቸው ከአገር አገር (ከሥርዓት ሥርዓት) መለያየት ብቻ ሳይሆን የተለየ እውቀትንም ይጠይቃሉ ። ስለሆነም እነዚህን የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች የሚነፈግና በእነርሱ የማይገዛ ሕብረተሰብ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕን ከመንፈጉም ሌላ የዚያኑ ያህል ፍትሕን ያጓድላል ።

## የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ጀይ ኤስ ዲ ዲግሪ ።
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፋኩልቲ - ጸሐፊው በዚህ ጽሑፍ ረቂቅ ላይ ለተደረገለት የተለያዩ ገንቢ ሀሳቦች ምስጋናውን ያቀርባል ።

1. ምንም እንኳን ቅጣት በሠፊው ማኅበራዊ ስሜት ኅብረተሰብ በአንድ አፈንጋጭ ላይ የሚወስደውን እርምጃ ሊያመለክት ቢችልም ፤ እዚህ ላይ የተጠቀምንበት ግን በጠባቡና በሕግ ትርጉሙ ፤ ከጥፋተኛነት ውሳኔ በኋላ የሚወስደውን እርምጃ በሚመለከት ረገድ ነው ።
2. ይህ ጽሑፍ እንደዊበሪያን አመለካከት ዋጋ ካላቸው ወጐችና ልማዶች ተገንጥሎ ሳይሆን ችግር ቀመስ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ዋጋ ያላቸው ወጐችና ልማዶች በተዋሐዱት መንገድ ምርምር ያደርጋል ። ጨዋነትንና ተራማጅነትን የመሳሰሉት ጽንሰ—ሀሳቦች ዋጋ ያላቸው ወጐችና ልማዶች የተዋሀዱቸው ናቸው ። ይህ ጽሑፍ የተጻፈበት ዓላማም ይህንኑ ለማሳየት ነው ፡ ጽሑፉ በሰው ልዕልና ላይ በተመሠረተ ሰብአዊና ትክክለኛ ሕብረተሰብ ላይ ያተኩራል ።
3. አንድ ሰው የሚጠቀምባቸው ምንጮች ፤ በምንጮቹ ብቁነትና መገኘት ይወሰናሉ ። የ1949ኙ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተጠቀሰበት ምክንያትም ጸሐፊው ከዚህ ሕግ ጋር ስለሚተዋወቅ ነው ። ሕብረተሰብን በአጠቃላይ ሁኔታ በሚያጠና እንደዚህ ባለ ጽሑፍ የአፍሪካና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ምንጮች አግባብነት ስላላቸው በተገቢው ቦታ ሁሉ ተጠቅሰዋል ።
4. ጂ.ኤ. ሆርኔት ፤ «ከለክ ፔይ ኤንድ ፕሮዳክቲቪቲ ኢን ሳውዝ አፍሪካ» ፤ ሳውዝ አፍሪካን ሬስ ሬሌሽንስ ፤ ሴፕቴምበር 1972 ፤ የድኅነት ገደብ መስመር (ፖቨርቲ ዳተም ላይን) በመሠረቱ ለመኖር የሚያስችል ምንዳዕ አይደለም ፤ ነፍስና ሥጋ ሳይለያዩ ለማቆየት የሚችል ብቻ መሆኑን ማስታዎስ ያሻል ። ኤስ.ጂ ሮጀርስ ፤ «አፓርታይድ ኤንድ ዘ አፍሪካን ወርከር» ፤ የተ.መ.ድ ዶኩዩሜንት ፤ ሜይ 1975 ።
5. ፍትሕ በሕገ—ፍልስፍና ፤ የራሱ ተቀጽላ ከሚያደርገው የሰው—ሠራሽ ሕግ (ፖዘቲቭ ሎ) አንፃር ሊታይ ይችላል ፤ ወይም ፍትሕ የሚመነጨው ሙሉ በሙሉ ከሕብረተሰቡ ነው ፤ ግቡም የሕብረተሰቡን ደኅንነት ማሻሻል ነው - በማለት አጠንክሮ ከሚናገረው «የሕብረተሰብ ደኅንነት ነቢብ (ቲዮሪ) አኳያ ወይም ፍትሕ የሰው—ሠራሽ ሕግ ተቀጽላ ሳይሆን የተፈጥሮ መብት ነው ፤ በተፈጥሮ ያለውን ወይም የሚገባውን መስጠት ነው ከሚለው «ከተፈጥሮ መብት ነቢብ (ቲዮሪ)» አኳያ ሊታይ ይችላል ። ብዙ የሕግ—ፍልስፍና ሥራዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ ። አቶ ቦርድ ፤ «ዘ አይዲያ ኦፍ ጀስቲስ» ለአጠቃላይ አቀራረብ ፤ እና ቢ.ኤ. ተማኖቭ ኮንቴምፓራሪ ቡርዣ ሊጋል ቶዎት ፤ ሞስኮ ፤ 1974 ፤ ለማርክሳዊ አመለካከት ፤ ያወዳድሯል ። ይሁን እንጂ ፍትሕ በፈለገው ዓይነት መንገድ ቢገለጽ በለውጥ መንገድ ላይ የሚጓዝ ሕብረተሰብ አንፃራዊ ጽንሰ—ሀሳብ ነው ። የሰው ልጅ በአዝጋሚ ለውጥ ወደፊትና ወደ ከፍተኛ ደረጃ በተጓዘ ቁጥር ፍትሕ አዲስና ሰፋ ያለ ትርጉም ይይዛል ።

6. አንድ ዋጋ ያለው ነገር (ቫልዩ) ለዘለዓለሙ በመጥፋቱ ፤ ድሮ የነበረውን ሥርዓት እንደነበረ ለመ መለስ የማይችልባቸው ለየት ያለ ባሕርይ ያላቸው ወንጀሎች አሉ ፤ ለምሳሌ ነፍስ ግድያ ወይም የሆነ የግል ተበዳይ ሳይሆን ነገር ግን በደሉ በአጠቃላይ በመንግሥት ወይም በሕብረተሰብ ላይ ሲፈጸም ፤ ለምሳሌ ስለላ ።

7. ጀርሚ ቤንታም ፤ ቤንታም (የ) ወርክስ ገጽ 399—402 ፤ (ለንደን ፤ 1843 ፤ ለከፍተኛና ዝቅተኛ ቅጣት አወሳሰን የተለያዩ የፖሉሲ ሚናዎች ።

8. የሐሞራቢ ሕግ አንድ ጌታ በባሪያው ላይ የነበረውን መብት በተካረረ ሁኔታ ደንግጓል ፤ ባሪያው በጌ ታው ላይ ግን ምንም መብት አልነበረውም ። አንድ ግንበኛ የገነባው ቤት ተደርምሶ የቤቱን ባለ ንብረት ልጅ ስለገደለ ተመሳሳይ ሀዘን እንዲደርስበት በማለት የግንበኛው ልጅ ተገደለ ፤ ለንጹሑ የግንበኛ ልጅ መስጠት ስለነበረበት ፍትሕ ምንም ዓይነት ጭንቀት አልነበረም ። ሊረጋገጥ በማይ ችል እምነተ—ቢስነት የተከሳሾች ሚስት ለባሏ መልካም ስም ስትል እራሱን ባሕር ውስጥ ጨምራ መስጠም ነበረባት ፤ ከሴትዮዋ ሕይወት ይልቅ መልካም ስም ትልቅ ዋጋ ነበረውና ። ይሁን እንጂ የሐሞራቢ ሕግ ደካማውን ክብርቱው ለመጠበቅና ባሏ የሞተባትን ሴትንና የሙት ልጅን ጽኑነት ለመጠበቅ የታለመ ነበር ብሎ መጥቀሱ ትክክለኛ ይመስላል ። እነዚህ ሕጐች በወጡበት ዘመን ለዚያ ሕብረተሰብ ተስማሚ ነበሩ ።

9. አንዳንድ የወንጀል ቅጣት ሊቃውንት ግለሰባዊውን ከአጠቃላዩ ለመለየትና የተለያዩ ዓላማዎች እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሯቸዋል ።

10. እንደቀድሞ ሕጐች ሳይሆን ዘመናዊ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለወንጀል በሙሉና በከፊል አላፊ አለመሆንን በአእምሮ አለመብሰልን ያሉትን የተለያዩ መከላከያዎችን በውስጡ ይዟል ። ይሁን እንጂ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኛነት የተፈጠረ ለወንጀል አላፊ አለመሆን ለመከላከያነት ሊቀርብ አይችልም ። አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ቁጥሮች ፤ 48 ፤ 49 እና 50

11. አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፤ 58 ፤ እና 59
12. ቁጥር 105 እና 107 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ያወዳድሯል ።
13. የዕድሜ ልክ እሥራት ሌላው ዓይነት ጽኑ እሥራት መሆኑ መታወስ አለበት ።
14. ፍራንሲስኮ አልባሬዝ ፤ ናሬቲቭ ኦፍ ዘ ፖርቱጊዝ ኤምባሲ ቱ ኢትዮጵያ ዲዩሪግ ዘ ይርስ 1520—1527 ፤ ገጽ 335 ፤ ኒውዮርክ ፤ 1881 ።
15. ሪቻርድ በርተን ፤ ፈርስት ፋትስቴፕስ ኢን ኢስት አፍሪካ ፤ ገጽ 190 ፤ ለንደን ፤ 1886 ።
16. ማርጀሪ ፐርሐን ፤ ዘ ገቨርንመንት ኦፍ ኢትዮጵያ ፤ ገጽ 194 ፤ ለንደን 1969 ።
17. ሳሙኤል ጐባት ፤ ጀርናል ኦፍ ስሪ ይርስ ሪዚዳንስ ኢን አቢሲኒያ ፤ ገጽ 336 ኒውዮርክ ፤ 1851
18. ፐርሐም ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 148
19. ፓውል ሐርተልሜር ጐልደን ላየን ፤ ገጽ 172 ፤ ለንደን 1965
20. ቁጥር 3 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1923 ።
21. ቁጥር 120—ሀ ። የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
22. ስቴቨን ሉዊንስተን ፤ ዘ ፒናል ሎ ኦፍ ኢትዮጵያ ገጽ 340 ፤ አዲስ አበባ 1965 ።
23. ዣን ግራቨን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ የኢትዮጵያ ሕግ መጽ ሔት ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 2 ገጽ 248 ።
24. ቁጥር 635 እና 637 በተከታታይ ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
25. የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ቁጥር 256 ፤ 445 ፤ 474 እና 479—481 በድንጋጌ ቁጥር 45/1953 ተጨመሩ ። ሌሎች በአብዮታዊው የ1976 ዓ.ም. ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተጨም ረዋል ።

26. ቁጥር 120—ሀ ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
27. በአካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት በምንነጋገርበት ጊዜ ስለማሰቃየት (ቶርቸር) ለማውሳት መገፋፋ ታችን አይቀርም ። ምንም እንኳን ቶርቸር የራሱን የሰውን ልጅ ያክል እድሜ ቢኖረውም በአሁኑ ጊዜ በገቢር ላይ መዋሉ የጨመረ ይመስላል ። የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ቶርቸር «የዘ መናችን ክስተት» አድርጐ ይመለከተዋል ። አንድ ሰው በተብራራ ሁኔታ ስለቶርቸር ሲያትት «ቶርቸር በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በ4ኛው ምዕተ— ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በሠፊው ጥቅም ላይ መዋሉ ከአሳዛኝ ሐቆች አንዱ ነው ።» ይላል ።ይህን አባባል በአንድ ሰለሰብአዊ መብት ጉዳይ አግባብ ባለው ዓለምአቀፋዊ ድርጅት የታተመ ስታስቲክሳዊ መረጃ በመጥቀስ ያጠናክረዋል ። (ታይም)(የ) መጽሔት ፤ አገስት 16 ፤ 1976 (ከዚህም በላይ ቶርቸር ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር አብሮ ስላደገ የተራቀቀ መሣሪያ በመጠቀም በአንድ ግለሰብ አካል ላይ የጭ ካኔ ጠባሳ ወይም ምልክት ባለመተው ሕይወቱን እስኪስት ድረስ ማሰቃየት ይቻላል ። ይሁን እንጂ ቶርቸር ከዚህ ጽሑፍ ዓላማ ውጭ ነው ። በመሠረቱ ቶርቸር የቱን ያህል በሠፊው በገቢር ላይ ቢው ልም ከጥፋተኛነት ውሳኔ በኋላ የሚጣል ቅጣት ሆኖ በይፋ አይሠራበትም ፤ ነገር ግን ከፍርድ ውጭ ወይም ቅድመ—ፍርድ ላይ አስገድዶ ቃል ለመቀበል ይሠራበታል ። በሰው ልጅ ዕድገት ውስጥ እንደ ባርነትና እንደአብዛኛዎቹ በአካል ላይ የሚፈጸሙ ቅጣቶች ቶርቸርም በታሪክ ብቻ የሚታወስ በት ጊዜ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

28. ሩሽ እና ኪርችሽሜር ፤ ፓንሽመንት ኤንድ ሶሻል ስትራክቸር ፤ ገጽ 21—22 ፤ ነው ዮርክ 1937 ።
29. ቁጥር 116 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1747 ።
30. አፍሪካ (የ) መጽሔት ገጽ 17 ፤ ማርች 1975 ።
31. የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳይ መምሪያ ፤ የተ.መ.ድ ፤ ካፒታል ፓንሽመንት ፤ የተ.መ.ድ ጽሑፍ ኤስ ቲ (ኤስ ኦ ኤ) ኤስ ዲ) 9 ገጽ 28—30 ፤ ኒውዮርክ 1962 ዓ.ም
32. ግራሽን ፤ ከላይ የተጠቀሰ ገጽ 289 ፡
33. የውኒዮርክ ስቴት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጊዜያዊ አሻሻይ ኮሚሽን ዘገባ (1965) በሎዊንስተን ውስጥ እንደተጠቀሰ ፤ ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 337—38 ።
34. ሎዊንስተን ፤ ከላይ የተጠቀሰ ።
35. ሆልና ግላክ ፤ ክሪሚናል ሎ ኤንድ ኢንፎርስመንት ፤ ገጽ 17 ኒውዮርክ ፤ 1958 ።
36. ሴሊን ፤ ዘ ዴዝ ፒናሊቲ ገጽ 15—77 ፤ ኒውዮርክ ፤ 1959 ።
37. በተ.መ.ድ ዘገባ የተጠቀሰው «የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ» በዚህ ምዕተ—ዓመት ለአዲስ ዓለምአቀፋዊ ሥርዓት የሚደረገው ትንቅንቅና ትግል ያስከተለው ሁኔታ ሆኖ ነው መታየት ያለበት። የዓለም ጦርነቶች ፤ «የቁጡ» መንግሥታት ከሥልጣን ላይ መውጣት ፤ አዳዲስ ነፃ መንግሥታት በሶስተኛው ዓለም ብቅ ማለታቸውና የነዚሁ መንግሥታት የፖለቲካ ቁንጮ ሰዎች ለተቀዳጁት አዲስ ነፃነታቸው (ምናልባትም ለግል ሥልጣናቸው) ቀናኢ መሆን ፤ ይህንኑ «የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ» ገጽታ ይፋ አወጣው ፡ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳዮች መምሪያ ፤ ከላይ የተጠቀሰ ።
38. አፍሪካ (የ) መጽሔት ፤ ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 16 ፤
39. ችግሩን ሰፋ አድርገን ስንመለከተው ደግሞ ብዙዎች የአፍሪካ መንግሥታት ይህንኑ የጥቂቱን ነጮች መንግሥት ለተቃዋሚዎቻቸው የላላ ሕግን እንዳያወጣ ለመጠየቅ እንዳይችሉ ከፍተኛ የሞራል ገደብ አለባቸው ፤ ምክንያቱም እነርሱም ቢሆኑ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ተመሳሳይ የጭካኔ ተግባር መፈጸማቸው ሊካድ የማይችል መራራ እውነት ስለሆነ ነው ። አፍሪካ መጋዚን ኤቢድ ገጽ 17
40. የተ.መ.ድ. ጽሑፍ ፤ ኤስ ቲ(ኤስ ኦ ኤ) ኤስ ዲ) 2 ፤ እና ኤን ሐይነር ፤ ሴንቴሲግ ባይ አን አድሚኒ ስትሬቲብ ቦርድ ኢን ሎ ኤንድ ኮንቴምፖራሪ ፕሮብሌምስ ፤ ቅጽ 23 (1958 ) ።
41. ቁጥር 88 ፤ 102 ፤ 122 እና 123 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
42. ኤን.ኤስ. ቲማሾፍ «ዘ ዳች ፕሪዝን ሲስተም» ኢን ጆርናል ኦፍ ክሪሚናል ሎ ፤ ክሪሚኖሎጂ ኤንድ ፖለቲካል ሳይንስ ቅጽ 48 (1958)
43. ኒውማን ፤ ሰርስ ቡክ አን ፕሮቤሽን ፤ ፓሮል ኤንድ ፓርደንስ ፤ ኒውዮርክ ፤ 1964 ፤ ሬክለስ ፤ ዘ ክራይም ፕሮብሌም ፤ ኒውዮርክ ፤ 1961 ፤ ኔሐራዐል ፤ ዘ ሶቪዬት ጁዲሻል ሲስተም ፤ ሞስኮ 1975 እና ሩሽ እና ኪርችሽሜር ፤ ከላይ የተጠቀሰ ያውዳድሯል
44. ኖርቢል ሞሪስ ፤ ዘ ፊውቸር ኦፍ ኢምሪዝንምንት ፤ ችካጐ ፤ 1957 ።
45. ወልተር ሬክለስ ፤ ዘ ክራይም ፕሮብሌም (3ኛ እትም 1961) ።
46. ይህ ጉዳይ ሰብአዊ መብትን የሚመለከት ከፍተኛ ቁም ነገር በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ በሕብረተሰብ መሠረታዊ ሕግ ውስጥ ይገኛል ፤ ሕገ መንግሥትም ውስጥም ቦታ ሊሰጠው ይችላል ። ዓለም አቀፋዊው የሰው ልጆች መብት ዲክላሬሲዮን (1948) የተለያዩ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ጉዳዮችን ይዟል ።
47. ቁጥር 2(1) ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
48. ይህ ግምት በከፊል በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ፤ 1754 ቁ. 42 ይገኛል ።
49. ቁጥር 136 (1) ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ፤ 1954 ።
50. ቁጥር 181—196 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 1954 ።
51. እነዚህ መብቶች በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 1954 ፤ በተለያዩ ቁጥሮች ሰፍረው ይገኛሉ ።
52. የተፈጥሮ ዕውቀት የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል መስሎ ሊታይ ይችላል ፤ ይሁንና ይህ ሁልጊዜ ሥራ ላይ ውሎ አያውቅም ። ሌክስ ታሊዮኒ የአንድ ሰው ሚስትና ልጆች ላለበት ዕዳ ተከፋይ በመሆን ለባለገንዘቡ ባሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ለባለገንዘቡ እንዲሰጡ አጠቃላይ በሆነ መንገድ ይደነግጋል ። የታወቀው የሀሞራቢ ሕግ ግንበኛው የገነባው ቤት ተደርምሶ የቤቱን ባለንብረት ልጅ ሲገድል የግንበኛው ልጅ እንዲገደል ደንግጓል ። 4ኛውን ምዕተ— ዓመት በሚመለከት ረገድ በፋሲል ናሆም ውይይት የተደረገበትን የ1957 ዓ.ም. በኤርትራ ስለሽፍቶች የወጣ ሕግ ፤ የኤርትራ ሕግጋት እንቆቅልሽ ፤ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ቅጽ 9 ቁ.2 ገጽ 258 ይመለከታል ።
53. ይህ ጉዳይ በ1947ቱ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 2 «በሕግነቱ መሠረት» ውስጥ ይገኛል ። ይሁን እንጂ በአንድ ጥፋት ሁለት ጊዜ መቅጣት ቢከለከልም ፤ የሕጉን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል የተለያዩ ቅጣቶች በአንድ ላይ ተደምረው ይጣላሉ ተብሎ በግልጽ በሕግ የተሰጠውን አያግድም ። ለአጠቃላይ ውይይት ፤ በሶቪዬት ሕብረት ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ፤ ቢ. ቴሬቢሎቭ ዘ. ሶቪዬት ኮርት፤ ፕሮግሬስ አታሚዎች ሞስኮ 1773 ይመለከታል ።